# የሰምርኔስ ቤት ክርስትያን ዘመን

እጅግ የተከበርክ አባት ሆይ፡ በማንነታችን የማይሞት ህይወት መኖሩን ስላወቅን ዛሬ ምሽት በጣም ደስ ይለናል። የአምላካችን ሕይወት እንደ እሳት ልሳን በእያንዳንዳቸው ላይ ወረደ፡ ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው መንፈስ ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች መናገር ጀመሩ። አባት ሆይ፡ እራስህን ለቤተ ክርስቲያን እንዲህ ቆርስህ ስለ ሰጠህ እናመሰግንሃለን። ጌታችንም "እኔ በአብ እንዳለሁ፡ አብም በእኔ እንዳለ፡ እኔም በእናንተ እንዳለሁ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ፡ ያን ቀን ታውቃላችሁ፡" ማለቱ አይደንቅም። የሰማይ አምላክ በሕዝቡ ዘንድ እንዴት አደረ! "ትንሽ ጊዜ አለ ከእንግዲህ ዓለም አያየኝም፡ እናንተ ግን፡ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ጋር ስለምሆን፡ በውስጣችሁም ስለምኖር ታዩኛላችሁ።" በሁሉም የቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ ትላንትና፡ ዛሬም፡ ለዘላለምም ያው ሆነህ እዚህ ትኖራለህና፡ በምትሰራው ስራ እናውቅሃለን። "ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል።"

2 ጌታ ሆይ፡ የዘመናት ሁሉ ጠርዝ—አልቆ ስናየው፡ ጊዜ አልቆ ዘላለማዊነት ሊጀመር መዘጋጀቱ ነውና። እግዚአብሔር አባት ሆይ፡ በህይወታችን ስላለ ዓላማ እና የልባችን አሳብ ስናየው፡ ህይወታችንም ስንመለከተው መንፈስ ቅዱስ መሪነቱን ሲረከብ ስናይ፡ ዛሬ ቅሪቶች በሚኖሩበት ዘመን፡ እንደምንኖር በማወቃችን በጣም ደስ ብሎናል። እግዚአብሔር ሆይ፡ ዛሬ ማታ በመለኮታዊ መገኘት ያሉትን ሰዎች ሁሉ እነዚህን የምንኖርባቸውን የቤተክርስቲያን ዘመናት አውቀው ፈጥነው ወደ ጌታ ኢየሱስ ይሽሹ፡ እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈ፦ "የእግዚአብሔር ስም የጸና ግንብ ነው፡ ጻድቅ ወደ እርሱ ሮጦ ያመልጥበታል፡" ነውና።

3 አምላክ ሆይ፡ ዛሬ ምሽት መጥተህ ማንነታችንን ቅባው፡ ጌታ ሆይ። ግራ የተጋቡትን፡ ጌታ ሆይ፡ የተቅበዘበዙትን አምጣቸው፡ ጌታ ሆይ፡ ምስኪን በጎችን ተመልከታቸው፡ የእረኞች ጥሪዎች ከየቦታው በዝተዋልና፡ ምን ማመን እንዳለባቸው አያውቁምና። አባት ሆይ፡ የታላቁ የበጎች እረኛ፡ የጌታ ኢየሱስ ታላቅ መንፈስ፡ ዛሬ ማታ እንዲህ እያለ ሲናገር እንዲሰሙ፡ እንጸልያለን፦ "ልጄ ሆይ፡ ወደ እኔ ና እኔም ስንበትን እሰጥሃለሁ፡ ይህም ወደ ዘላለማዊ መዳረሻህ የምትታተምበት ዕረፍት ነው፡" ሲል ይሰሙት። ጊዜው እያለቀ እንደምናየው በምድር ላይ አይቅበዝበዙ። ስማን፡ ጌታ ሆይ። በተናጋሪው ተናገረን፡ ሁላችንም እንሰማሃለንና፡ በሚሰሙ ጆሮዎች አንተ ሰማ። በኢየሱስ ስም እንጸልያለን። ኣሜን።

4 ተቀመጡ። አሁን፡ ዛሬ ማታ የምንማረው ሁለተኛው የቤተክርስቲያን ዘመን ነው። ብዙዎቹ ማስታወሻዎችን እና ነገሮችን ሲይዙ አይቻለሁ፡ በእያንዳንዱ ጊዜ ይህንን ግልፅ ማድረግ የምፈልገው ለዚህ ነው።

5 እንግዲህ፡ ሁለተኛው የቤተክርስቲያን ዘመን የሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ተብሎ ይጠራል። የሰምርኔስ ዘመን፡ ሰፍራውን የተቆጣጠረው፡ የኤፌሶን ዘመን በወጣበት በተመሳሳይ ጊዜ ነው። የኤፌሶን ዘመን **እ.ኤ.አ** ከ 55 እስከ **እ.ኤ.አ** 170 ነበር። የሰምርኔስ ዘመን ከ170 ይጀምራል እስከ 312

ይዘልቃል። ይህች ቤተ ክርስቲያን የተሰደደች ቤተ ክርስቲያን ናት፡ የሰማዕቱን አክሊል የምትጎናጸፍ፡ የመከራ ቤተ ክርስቲያን ናት። ለምርጧ ቤተክርስቲያን፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተገባላት ቃል ኪዳን፡ የህይወት አክሊል ነው።

6 እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር እጅ የተያዘ የየራሳቸው **ኮከብ** ነበረ፡ እርሱም የዚያን ዘመን ቤተ ክርስቲያን “መልእክተኛዋ” ነው። ከሌሎቹ ይልቅ የማውቀው በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ዘመን የነበረው መልእክተኛ ነው (መጽሐፍ ቅዱስ እነማን እንደሆኑ አይናገርምና) እርሱም ጳውሎስ ነበር፡ ኤፌሶን ቤተ ክርስቲያንን ተክሎ የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋይም ነበርና፡ ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ ብርሃን ይዞ የመጣው እርሱ ነበር፡ ከእርሱ በኋላም ቅዱስ ዮሐንስ አስቀጠላት። ከዚያም ፖሊካርፕ ነበር፡ እያለ ይቀጥላል... ከዚያም ፖሊካርፕ፡ ቀጠለ፡ ማለቴ ነው።

7 አሁን፡ በሰምርኔስ ዘመን፡ ፈልጌ እንዳገኘሁት... ኢራኔዎስ እንደነበረ፡ በሙሉ ልቤ አምናለሁ። እና አሁን ከፖሊካርፕ ይልቅ ኢራኔዎስ የመረጥኩበት ምክንያት ልነግራችሁ እፈልጋለሁ። አሁን፡ ብዙዎች የሐይማኖት መሪዎች (እና የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪዎች) መልእኩ ፖሊካርፕ ነው ለማለት ይፈልጋሉ። ፖሊካርፕ የቅዱስ ዮሐንስ ደቀ መዝሙር ነበር፡ እውነት ነው። ፖሊካርፕ ምስክርነቱ... በ—በሰማዕትነት አተመ፡ በቀጥታ ልቡን ወግተው ገደሉት። እንግዲህ፡ እጅግ ታላቅ ሰው ነበረ፡ እግዚአብሔርን የሚፈራ፡ መልካም፡ እንጋፋ ሰው ነበር። እስካሁን ካየናቸው ታላላቅ ክርስቲያኖች አንዱ እንደነበረ ጥርጥር የለውም። ከህይወቱ እንከን ማውጣት አትችሉም።

8 ኢራኔዎስ የመረጥኩበት ምክንያት ግን፦ ኢራኔዎስ ከፖሊካርፕ በበለጠ ለቅዱስ ቃል ቅርብ እንደነበረ አምናለሁ። ፖሊካርፕ ግን ወደ ሮማውያን ድርጅት የማቋቋም ሃሳብ በመጠኑ ያጋደለ ነበርና። ኢ—ኢራኔዎስ ግን ፈጽሞ በማውገዝ፡ አጥብቆ ተቃወመ። እንደምናውቀውም፡ ይህ ጉዳይ፡ በኒቂያ ጉባኤ የተነሣ ታላቅ ነገር ነበረ፡ ከዋናዎቹ ጉዳዮች አንዱ እግዚአብሔር **ሦሰት** ነው ወይስ እግዚአብሔር **አንድ** ነው የሚል ነው። ኢራኔዎስም፡ እግዚአብሔር አምላክ፡ አንድ ብቻ ነው ከሚሉት ጎን ቆመ።

9 **ከቅድመ-ኒቂያ አባቶች** ጽሁፎች፡ ከአንደኛው ዕትም፡ ገጽ 412 ላይ፡ ትንሽ አንቀጽ ማንበብ እችላለሁ፡ በማስታወሻ መያዝ ከፈለጋችሁ፡ **ቅድመ-ኒቂያ አባቶች** አንደኛው ዕትም። በገጽ አሰራ ሁለት ላይ፡ እንግዲህ... ዕትሙን ከፈለጋችሁ፡ የሶስተኛው ዕትም የመጨረሻ ክፍል ነው። ሙሉውን ማንበብ ትችላላችሁ፡ በውስጡ በርካታ ምዕራፎች፡ ወይም በርካታ ዓረፍተ ነገሮች አሉ። አሁን በመጨረሻ ማንበብ እጀምራለሁ—በመጨረሻዎቹ፡ ሃያ ሠላሳ ስንኞች ላይ። ከፊሉን እንጂ፡ ሁሉንም አላነበውም፡

“ስለ ሰብዕናው የሚናገሩ ሌሎች መገለጫዎች በሙሉ... የአንዱ እና የተመሳሳይ ሰው መጠሪያ የሚያሰረዱ ናቸው፡” (እያችሁ፡ ‘አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ፡’ በማለት ስለሚጠሩት ነገር ለመናገር እየሞከረ ነው፡ እንዲህ በማለት፦ “እነዚህ የአንዱ ማንነት፡ **መጠሪያዎች** እንጂ፡ ሰዎች አይደሉም።” ዛሬም የምናስተምረው ይህንኑ ነው።) “ለምሳሌ፡ ያህል” (በቅንፍ ውስጥ) “(በእንግሊዘኛ)፡ **የኃይል ጌታ፡ የሁሉም ጌታ አባት፡ ሁሉን ቻይ አምላክ፡ ልዑል፡ ፈጣሪ፡ ሠሪ፡** እና የመሳሰሉት። እነዚህ የተለያዩ ተከታታይ

አካላት ሰዎች እና መጠሪያዎች ሳይሆኑ፡ የአንዱ እና የተመሳሳይ አካል ናቸው፡” (አሜን!) “አንድ አምላክ፡ አባት፡ በሚሆነው በሰሙ… በእርሱ—ሌሎች ነገሮች ሁሉ… ወደ መኖር… እንዲመጡ ባደረገው፡ የመኖር ምክንያት የሆነው ስም።”

10 ኢራኔዎስ እንዲህ ተናገረ “እነዚህ ሁሉ መጠሪያዎች የማንነቱ መጠሪያዎች ብቻ ናቸውና፡ በአንድ ስም፡ በአንዱ አምላክ ሥር ይጠቀለላሉ።” የሳሮን ጽጌሬዳ ተባለ። እንዲሁም ነውና። መጠሪያው ነው። የንጋት ኮከብ። አልፋ ተብለዋል። ኦሜጋ ተብለዋል። የሰብዕናው መጠሪያዎች ናቸው። አባት ነበረ። ልጅ ነበረ። መንፈስ ቅዱስም ነበረ። አምላክ ግን **አንድ** ብቻ ነው። አንድ አምላክ፡ ስሙም አንድ ነው። በምርመራው ሂደት—ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ሂደት ውስጥ ኢራኔዎስን ትክክል እንደሆነ ያሰብኩበት፡ ዋና ምክንያትም ይህ ነው።

11 ሌላው ላነብላችሁ የምፈልገው ነገር፡ **ሃው ዲድ ኢት ሃፐን**? በሚል መጽሐፍ ውስጥ ይገኛል፡ ይህ ደግሞ ከታሪክ ምሁራን ነው። እና፡ **ሃው ዲድ ኢት ሃፐን?** በአር. ሲ. ሃዘልታይን የተጻፈ፡ የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስትያን ታሪክ ነው። በገጽ 180 ላይ፦ “በኢራኔዎስ ዘመን የነበሩ መንፈሳዊ ስጦታዎች፡ **እ.ኤ.አ** ከ177 እስከ 202።” አሁን፡ ይህ የጠቀስኩበት ምክንያት፡ በቴፕ እየተቀዳ ስለሆነ ነው፡ እያችሁ፡ ከዚህ በ—በመቀጠልም በመጽሃፍ ይጻፋል፡

“የፈረንሳይ ሐዋርያዊ አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የነበራቸው በኢራኔዎስ ጊዜ ነበር።” ተመልከቱ፡ ይህም ከትምህርቶቹ ነበር። “በሊዮን ውስጥ የነበሩ የኢሬኔዎስ ቤተ ክርስቲያን አባላት፡” ሊዮን፡ ፈረንሳይ ነው፡ “በልሳኖች ይናገሩ ነበር። የሞተ ሰው ከሞት ሲነሳ ማየት የተለመደ ነበር። ፈውስ—በወንጌላውያን ሰራ ሁሉ በየዕለቱ ፈውስ ይሆን ነበር… በየቦታው በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት የሚከሰት ነገር ነበር።” ኢራኔዎስም እንዴት ማስተማር እንዳለበት የሚያውቅ ነበር! “ተአምራቶች ብዙ ጊዜ ነበሩ። እንደ እውነቱ ከሆነ፡ እነዚያ አብያተ ክርስቲያናት ያለ እግዚአብሔርን መገኘት ተአምራዊ መገለጥ ሆነው እያውቁም ወይም ያለ ራዕይ፡ የተፈጥሮ ነገሮችን፡ በተአምር ማገድ፡ ይህም በዘመኑ የነበሩትን ወንጌላውያን ክርስቲያኖችን ለማስታወስ ነው፡ የተወደዱ ደቀ መዛሙርቱ ነበሩ። ካለፉት ታሪኮች ግን፡ በመጀመሪያ የሮማ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሙታን የተነሱበት አንድም ምስክርነት ማግኘት አንችልም።”

12 ዎቹስ ሌላ ፍላጎት የሌላቸው… በሁለቱም ወገኖች የማይወግኑ፡ እውነትን ብቻ የሚናገሩ ሰዎች ናቸው። የታሪክ ተመራማሪዎች ናቸውና።

13 ምክንያቱ፡ ኢራኔዎስም፡ እንደሚመስለኝ ከሆነ፡ ጳውሎስ እና ደቀ መዛሙርት ያስተላለፉትን ያው እምነት በውስጡ ስለነበረች ነው። እኔም የሰምርኔስ መልአክ እሱ እንደነበረ… እንዳምነው ያደረገኝ ምክንያት ያ ነው፡ ምክንያቱ… ተመሳሳይ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ስለነበሩት፡ የእግዚአብሔር ቃል መሰረት ያደረገ ተመሳሳይ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሲኖር ሁሌም ተመሳሳይ ዓይነት ነገር ያፈራል። አብያተ ክርስቲያናት ምንም ቢሉ፡ ዝም ብላችሁ የእግዚአብሔርን ቀመር ተከትላችሁ ቃል በቃል ከኖራችሁ፡ እና በተነገረው መንገድ ከተከተላችሁት፡ ተመሳሳይ ዓይነት ነገር ያፈራል። ኢራኔዎስ ያደረገውም ያው ነው።

14 እንግዲህ፡ ፖሊካርፕን ብንወስድ፡ መልካም ሰው እንደነበረ እንረዳለን፡ ቢሆንም እሱ ልክ እንደኒቆላውያን ሰራ፡ ቤተ ክርስትያንን እንደ ተቋም ለማደራጀት የሚተጋ እንደነበረ ይታወቃል። ቤተ ክርስቲያንን በማደራጀት፡ ወ—ወንድማማችነትን ለማምጣት ይጥሩ ነበርና። በሰነ አእምሮ እውቀት መልካም ይመስላል፡ ይሁን እንጂ፡ ይህን እወቁ፡ እንደ—መንፈስ ማሰብ እስከማትችሉ ድረስ... መንፈስ ከሰነ አእምሮ እውቀት እጅግ ከፍ ያለ ነገር ነው። "አሳቤ ከአሳባችሁ ከፍ ይላል፡" ይላል እግዚአብሄር። "መንገዴም ከመንገዳችሁ ከፍ ያለ ነው።" ስለዚህ ይህን ለመከተል መንገዱ አንድ ብቻ ነው፡ እርሱም ንድፉን ብቻ ተከተሉት። ትክክል።

15 ለምሳሌ፡ ከዚህ ተነስታችሁ ብትሄዱ፡ ብለን እናስብ... ዛሬ ማታ ወደ ቺካጎ የምሄድ ከሆነ፡ ወጥቼ ኮምፓስ መግዛቴ አይቀርም፡ ከዚያም፡ "እሺ እስኪ እንየው፡ ቺካጎ መንገዱ በዚህ በኩል ነው። መልካም፡ ጉዞዬን እጀምራለሁ" እላለሁ። ከጄፈርሰንቪል ዘው ብዬ አልወጣም። አያችሁ? የጉዞው ካርታ መያዝ አለብኝና። እንዲሁም ስድስት እና ሰባት ሰዓታት በመኪና ተጉዤ—ቺካጎ የሚያስገባኝ የተዘረጋ... የመንገድ ዝርጋታ አለ፡ መንገድ መቊረጥ አልችልም። አውሮፕላን አቋራጭ መንገድ አይጠቀምም፡ መብረር የሚችልባቸው፡ እንዲቆይበት የተወሰኑለት ዲግሪዎች—የበረራ መስመር ወይም የተወሰነለት ከፍታ አለ።

16 የተሰራ መንገድ አለ፡ እግዚአብሔርም መንገድ አለው። እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያኑ፡ ለህዝቡ መንገድ አለው። በሊቃነ ጳጳሳት፡ ካርዲናሎች፡ ሊቀ ጳጳስ ወይም አጠቃላይ የበላይ ተመልካቾች ቁጥጥር ሥር፡ እንድትሆን አሰቦ አያውቅም። መንፈስ ቅዱስ ያሳድጋት ዘንድ፡ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ሞግዚት ነው። በቤተ ክርስትያንም ይሁን፡ በሌላም ነገር ሁሉ፡ ካርዲናሉን ወይም ካህኑን ቅዱስ ሰው ለማስደረግ—ቅድስናውን በሙሉ ወደ አንድ ሰው ብቻ አይሄድም። ምእመናንም እንዲሁ መብት አላቸው... እንደ ማንኛውም ሰባኪ ለመንፈስ ቅዱስ ባለ መብት ናቸው፡ እንደ ፓስተሩ፡ ዲያቆን፡ ባለ አደራ፡ ወዘተረፈ። ምእመናን!

17 **ኒቆላውያን** ብለው የሚጠሩበት ምክንያትም፡ ስለ **ኒቆላውያን**፡ ትናንት ማታ፡ የቃሉን ፍቺ፡ ከግሪክኛ አውጥተን እንዳየነው፡ ኒ-ቃ-ኦ፡ ይህ ማለት **ኒቃኦ**፡ ትርጉሙም "መውረር፡ ወይም ማሸነፍ ነው።" ማንን? ኒ-ቃ-ኦ፡ ኒቆላውያን፡ **ምእመናንን**፡ "ምዕመናንን መውረር፡" የሰዎችን የአገዛዝ ሹመቶችን በላያቸው ላይ በመስጠት ማሸነፍ፡ የሚመሯቸው እና የሚያስተምሯቸው ቀሳውስት፡ ሁሉም በአንድነት በመሆን ውሳኔን ያስተላልፋሉ። የኒቂያ ጉባኤ ሂደትም እንዲሁ ነበር። ምክንያቱ በኒቂያ ጉባኤ ብዙዎች ተሰብሰበው የአገዛዝ ሹመት በማድረግ ውሳኔን አስተላለፉ። አሁን አያስፈልገንም... በዚህ ርዕስ ላይ ብዙ ማውራት አያስፈልግም፡ ምክንያቱ ስለ ኒቂያ ጉባኤ፡ የሐሙስ ማታ ርዕስ ነው።

18 ይሁን እንጂ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስትያን የተመሰረተችው በዚያ ነበር፡ ከነ ቅዱስ ጳውሎስ፡ እና ከኢራኔዎስ፡ እና ከቅዱስ ማርቲን፡ እና በሌሎችም ምክንያት በተቀየሩ ሰዎች ምክንያት ተመሰረተች። ወደ ክርስትና የተለወጡ ነበሩ... ከአረማዊነት ወደ ክርስትና የተለወጡ ሰዎች ነበሩ፡ ነገር ግን ቤተ ክርስቲያንን ወደ ብሉይ ኪዳናዊ የአገልግሎት ዓይነት ሰርዓት ሊጎትቷት ፈለጉ፡ እንደ ሊቀ ካህናት መሾም፡ እና—የሐወርያዊ መተካካት አይነት፡ በአንዱ ጳጳስ

ሌላ ጳጳስ፡ በሌላ ጳጳስ መተካት ተመኙ። ይህን መጽሐፍ ቅዱስ በደንብ ስናጠናው፡ በትክክል እውነት መሆኑን እና እግዚአብሔር ነገሩን ከመጀመሪያው እንዴት እንደኮነነው ማወቅ እንችላለን፡ በትላንትናው ምሽት የቤተ ክርስቲያን ዘመን ውስጥ፡ "እጠላዋለሁ!" ብሎናል፡ ቤተ ክርስቲያንም ትጠላዋለች።

19 እግዚአብሔር ቤተክርስቲያንን በሰዎች እንድትመራ አስቦ አያውቅም። እግዚአብሔር ቤተክርስቲያኑን ይመራል፡ በመንፈስ ስጦታዎች ይመራታል። መንፈስን ለማረም የመንፈስ ስጦታዎች በቤተክርስቲያን ውስጥ አሉ። በቤተክርስቲያኑ ውስጥ አምስት የአገልግሎት ዘርፎች አሉ። በመጀመሪያ ደረጃ ሐዋርያት፡ ወይም፡ ሚስዮናውያን ናቸው። ከፍተኛው ጥሪ ሚስዮናዊነት፡ ሐዋርያነት ነው። **ሚስዮናዊ** የሚለው ቃል ትርጉም "የተላከ"፡ **ሐዋርያ** ማለት ትርጉሙ "የተላከ" ማለት ነው። ሚስዮናዊ ለመባል ለምን እንደመረጡ፡ እኔ አላውቅም። እነርሱ ግን ሐዋርያት ናቸው። እሺ። ሐዋርያት፡ ነቢያት፡ አስተማሪዎች፡ ወንጌላውያን፡ እረኞች። አሁን፡ እነዚህ እግዚአብሔር ለቤተክርስትያኑ የመደባቸው ዘርፎች ናቸው።

20 ከዚያም በእያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በሕዝቡ መካከል የሚመጡ ዘጠኝ መንፈሳዊ ስጦታዎች አሉ፡ ይህም፡ እውቀት፡ ጥበብ፡ የመፈወስ ስጦታ፡ ተአምራት ማድረግ፡ በልሳኖች መናገር፡ ልሳኖችን መተርጎም ናቸው። እና እነዚህ ሁሉ ነገሮች በእያንዳንዱ የአጥቢያ አካል ውስጥ ይገኛሉ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚኖር እያንዳንዱ ሰው የግል አገልግሎት አለው፡ እና ይህ የግል አገልግሎት የኢየሱስ ክርስቶስን አካል ለማነጽ ከተቀረው አገልግሎት ጋር፡ አብሮ ይሄዳል። እና በጭራሽ...

21 አሁን፡ እዚህ ላይ፡ አስታውሱ... ዛሬ ማታ እነዚህን መስመሮች እስላለሁ። የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ኤፌሶን፡ ሰምርኔስ፡ ጴርጋሞን፡ ትያጥሮን፡ ሰርዴስ፡ ፊልደልፊያ፡ ሎዶቅያ። አሁን፡ **ይህ** ሲቀጥል፡ ይህች የመንፈስ ሙላት የነበራት ቤተ ክርስትያን እንደነበረች አስታውሱ፡ በቤተ ክርስቲያን ዘመን መጨረሻ ላይ ግን ይህ ተጨምቆ ወጥቶ እናየዋለን። **እዚህ** ያለችው ይህችኛዋ፡ አንሣ እስክትደቅቅ ድረስ፡ ቀጣይ ቤተ ክርስትያን ዘመን በትንሽ፡ በትንሹ እየተጨመቁ ቀጠሉ። አቤት፡ ወደ ትያጥሮን ቤተክርስትያን ዘመን ስንደርስ! "የምነቅፍብህ ነገር አለኝ፡" ይለዋል።

22 አሁን፡ ያን ካለፈ በኋላ፡ እግዚአብሔር ማርቲን ሉተር የተባለውን ጀርመናዊ ሰው አስነሣና ቤተ ክርስትያንን እንደገና ወዘወዛት። በትንሹ ተጨማሪ ነገር ጀመረ፡ ሰለ ጽድቅ ሰበከ፡ ማርቲን ሉተር ከመጣ በኋላ፡ ሰለ ጽድቅ ሰብኳል። ከዚያም ጆን ዌሰሊ መጣና ቅድስናን ሰበከ። ከዚያም **በዚህችኛዋ** የቤተክርስቲያን ዘመን ላይ፡ እየተላለፈ ከመጣው ከተመሳሳይ ድንቆች እና ምልክቶች ጋር፡ እንደገና በቀጥታ፡ ወደ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ደረሱ። በአስራ አምስት መቶ ዓመታት የጨለማ ዘመን ውስጥ ሲተላለፍ ከቆየ በኋላ የወጣው **በዚህች** በኩል ነው። እና በአብያተ ክርስትያናት ዘመናት ውስጥ... ረጅም እና እጅግ የጨለመ ጊዜ የሚሸፍን ቤተ ክርስትያንም ያ ነው። ከዚያ የጽድቅ፡ የቅድስና፡ እና የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ መምጣት የሚጀምርበት መንገድ **ከዚሁ** ነው። መጽሐፍ ሲናገር፡- "**በዚህ** ዘመን መጨረሻ ላይ፡ ትንሿን መንጋ የሚያጨናንቃት ነገር ይጀምራል ምክንያቱም የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን ኒቆላውያን ያኔ የጀመሩት ተመሳሳይ ነገር፡ **እዚህም** ማድረግ ትጀምራለች።"

(አምላክ ሆይ፡ ወደዚያ እስክደርስ ድረስ አፌን ልዝጋ።) አያችሁ ወይ? እኔ እየዋለሁ። እዚህ ውስጥ ማየት እስክትችሉ ድረስ፡ ተመልከቱ። እናም የዚህች ዘመን የቤተ ክርስቲያን መልእክተኛ የሐይማኖት ተቋማትን እንደሚጠላ አሳያችኋለሁ። በኋላም መንፈስ በልጆች ላይ ትንሳኤ ይሆናል። ሁሌም እንደዚያ ነውና። አሁን እንኳ ሳይቀር...

23 አሁንም፡ ይህን አስተውሉት፡ እዚህኛው ጋር እንዴት ያለ ታላቅ ነገር የነበረ፡ ደበዘዘና፡ በመጨረሻው ፈጽሞ ተዳፈነ። ከዚያም እንደገና ጀመረ። በሉተር እንደገና መለሰው፡ ጽድቅ፡ ቅድስና፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ ከዚያም ልክ የዘመን ፍጻሜ ሲሆን፡ ይሄኛው ፈጽሞ እስኪጠፋ ድረስ፡ እጅግ አነስተኛና ጥቂት እስክትቀሩ ድረስ፡ እንደገና ማዳፈን ይጀምራል፡ "ስለተመረጡት ሲል ሥራውን ካላሳጠረው በቀር፡ የሚድን ሥጋ እንደማይኖር" የሚናገረውም ያኔ ነው። አያችሁ? ይኸውላችሁ፡ በዘመን ፍጻሜ ውስጥ ነን። ይህን በልባችሁ ውስጥ ያዙ።

24 አሁንም የሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን ዘመን እንጀምራለን። በመጀመሪያ እኔ በያዝኩት በዚህ ወረቀት ላይ—እዚህ መከፋፈል እፈልጋለሁ። አሁን፡ ሁለተኛው የቤተክርስቲያን ዘመን ሰምርኔስ ናት፡ ሁላችሁም ከእኔ ጋር ትስማማላችሁ ብዬ (ተስፋ አደርጋለሁ፡ ወይም በመጠኑም ቢሆን፡ በከፊል) ኢራኔዎስ የዚህ ቤተ ክርስትያን ዘመን ኮከብ መሆኑን ትስማማላችሁ ብዬ አምናለሁ። የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነበር ምክንያቱ እስከ ፈረንሣይ ድረስ፡ እስከ (ጓል) ድረስ፡ አገሩን ሁሉ አዳርሶታልና፡ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን አቋቁሟል፡ እያንዳንዳቸውም በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ላይ የተመሰረቱ፡ በልሳን መናገር፡ ሙታንን ማስነሳት፡ የታመሙትን መፈወስ፡ ዝናብን ማቆም፡ እና በየቀኑ ተአምራትን ማድረግ ነበራቸው። ሕያው አምላክ በሰዎች መካከል እንደሚኖር ያውቁ ነበር። ያ የእግዚአብሔር ሰው ነበር፡ ኢየሱስም እንደተናገረው፡ "እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ በቀር... " ማለቴ፡ ሰዎች—እንደተናገሩት፡ "እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ በቀር ማንም ሰው እነዚህን ሥራዎች ሊሠራ አይችልም።" ኒቆዲሞስ ለኢየሱስ የተናገረው ነገር ነው።

25 አሁን፡ ወደ ሊዲያ እና ወደ ምዕራብ የንግድ መውጫ፡ የነበረች የንግድ ከተማ ናት። በእስያ ውስጥ ሦስተኛው ትልቁ ከተማ፡ ታላቅ የወደብ ከተማ ነበረች። በሀብት፡ በቤተ መቅደሶች፡ በህንጻዎች፡ በትምህርት ቤቶች፡ በሕክምና እና በሣይንስ የምትታወቅ ነበረች። አይሁዶች በ—በሰምርኔስ ይኖሩ ነበር፡ የሰምርኔስንም ሕዝብ ሰበኩ። ፖሊካርፕ የሰምርኔስ የመጀመሪያው ቢሾፕ ነበር። ፖሊካርፕ እና ሌሎች ታማኝ አገልጋዮች የእግዚአብሔርን ጥልቅ እምነት ባመኑት የሰምርኔስ ሰዎች ላይ አጸኑት። የቀደሙት የቤተክርስቲያን አባቶች ለሰምርኔስ እውነትን መክረዋል።

26 የሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ የቤተ ክርስቲያኒቱ ስም ሰምርኔስ ነበር፡ **ሰምርኔስ፡** ይልቁንስ፡ ትርጉሙ "መራር፡" ከርቤ ማለት ነው። ከመሞት ጋር የተያያዘ ነው፡ ይገደሉ ነበርና።

27 የተሰደደች ቤተ ክርስቲያን ናት፡ እግዚአብሔርም "የተሰደደች" በማለት ይጠራቸዋልና። እግዚአብሔር ሰደታቸውን ተመለከተ፡ እና የሚሸከሙበትን ጸጋ ሰጣቸው። መከራቸውን አይቶ፡ በሞት ላይ ድል ሰጣቸው። ድህነታቸውን

አይቶ፡ በእርሱ ዘንድ ባለጠግነትን ሰጣቸው። የሰምርኔስ ቤተክርስቲያን በመከራ እቶን ውስጥ አለፈች፡ ለእርሱ ግን ጣፋጭ የመዓዛ ሽታ ነበረች። ይህ ማለት ግን ቅሪቶችን ናቸው፡ መላው የሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን ማለቴ አይደለም፡ የምናገረው ስለ ቅሪቶች ነው። ታላቁ **አሰር የመከራ ቀናት** ማለት "አሰር ደም አፋሳሽ የሰደት አመታት ናቸው።"

28 ይህን ሰው የሰሙን ፊደል መቁጠር፡ ወይም መጥራት፡ ልቻል አልቻል አላውቅም። ይህ የዚያን ጊዜ የነበረ ንጉሠ ነገሥት፡ ከኔሮ ከ67 በኋላ ከነበሩ ሁሉ ይልቅ ደም አፍሳሽ ነበር ብዬ አምናለሁ፡ ዲ-ዮ-ቅ-ላ-ጢ-ያ-ኖ-ስ። **እ.ኤ.አ** ከ303 እስከ 312 ዓመታት የነበረ ነው።

29 እግዚአብሔር ሰምርኔስን፡ እንደ እርሱ እስከ ሞት ድረስ ታማኝ እንድትሆን አጥብቆ ይመክራታል፡ "እብም ለእኔ እንደ ሰጠኝ፡ እኔ ደግሞ የሕይወትን አክሊል እሰጣችኋለሁ።" እግዚአብሔር ድል ነሺውን (በመከራ ውስጥ) በሁለተኛው ሞት ላይ ድል እንደሚቀዳጅ ቃል ገባለት፡ "ሥጋን የሚገድሉትን አትፍሩ፡ ነገር ግን ነፍስን የሚያጠፋ፡ ወይም፡ ነፍስን የሚገድለውን ፍሩ።" ይህም... የሰምርኔስ ሰዎች እስከ መጨረሻው ድረስ መጽናት ያሰፈልጋቸው ነበር፡ "ሰዎችን አትፍሩ፡ የሕይወትም አክሊል ይሰጣችኋል።" በዘመናት ውስጥ የነበረውን የክርስትና ሰደት በቤተ ክርስትያን ዘመናት የተጻፉ ናቸው፡ የሰምርኔስም፡ እጅግ አስፈላጊ ነው። ጌታ ቢፈቅድ፡ ቶሎ ብለን ወደዚያ ማለፍ እንፈልጋለን።

30 አሁን፡ በክፍሉ ላሉ ለሌሎቹ በፍጥነት እየጻፍኩላቸው ስለሆነ... ምናልባት አንዳንዶቻችሁ ጥቂት ነገሮች ካመለጣችሁ፡ እንዲህ እናደርጋለን... ከእኛው ዘንድ... በፈለጋችሁ ጊዜ በእርግጠኝነት ማግኘት ትችላላችሁ፡ እነዚህን ለእናንተ በመሰጠታችህን—ደስታ ይሰማናል። (ይቅርታ።)

31 አሁን ከ2ኛው ምዕራፍ 8ኛው ቁጥር፡ ዛሬ ማታ እንጀምራለን። አሁን፡ ስለ ትናንት ማታ ምን ላይ ነበር ያቆምነው? እሱ ኒቆላውያንን... በትክክል መጥላቱ። አይደል? አሁንስ እግዚአብሔር ምን አደረገ? ከሁሉ በፊት ማወቅ ያለብን ነገር ምንድነው? የኢየሱስ ክርሰቶስ መገለጥ፡ ማን እንደሆነ እና ምን እንደሆነ ነው። ከዚህ በመቀጠል ታላቁ ነገር፡ ከሱ ሌላ ቤተክርስቲያኑን የሚገዛ ማንኛውንም ነገር እንደሚጠላ ተረድተናል። ቀናተኛ አምላክ ነው።

32 እዚህ ጋር ቆም ባደርገው ደስ ይለኛል፡ ምክንያቱ እዚህ ጋር ጥቂት ነገር ለመጥቀስ ያህል፡ አራት ጥቅሶችን ይዘናል። በመልካሙ ነቢይ በሳሙኤል ጊዜ፡ እስራኤላውያን ሁሉ፡ እንደሌላው ዓለም መሆን ሲፈልጉ ሰንቶቻችሁ ማስታወስ ትችላላችሁ? ትዝ ይላችኋል? ነብዩም "ሰታችኋል፡" በማለት፡ ነግሯቸው ነበር! እነርሱ ግን እንደ ፍልስጥኤማውያን፡ እና እንደ ተቀረው ዓለም—እንደ ሌሎች መሆን አማራቸው። እንግዲህ፡ በዚህኛው በመጀመሪያ የቤተ ክርስቲያን ዘመን የሆነውም ያ ነው። ሰዎች እግዚአብሔር እንዲመራቸው አለመፈለጋቸው ይገርማል። ሌሎችን መከተል ይፈልጋሉ... ሰው ይፈልጋሉ። እስራኤል፡ ከመቼውም ጊዜ በላይ የላቀውን ሰህተት የሰራው፡ ያኔ ነው... አስቀድሞ በጸጋው ነብይ፡ እና መሪ ሰጥቷቸዋል፡ የማስተሰረያ የበግ ጠቦትም ሰጥታቸዋል፡ ከሰማይም ምግብ ሰጣቸው፡ ጸጋው የሚያቀርብላቸው የበጎ ሰጦታዎች ሁሉ ሰጣቸው፡ እነርሱ ግን፡ በዘጸአት 19 ላይ፡ ሕግን ተመኙ።

የሰነ መለኮት ዶክተሮችን፡ እና አንዳንድ ሰዎች እንዲኖሯቸው ተመኙ፡ በዚያ ውስጥም፡ አንድ ነገር መጨመር ፈለጉ።

33 ሰው ሁል ጊዜ ከፈጠረው ፈጣሪ ይልቅ ለመብለጥ ይሞክራል፡ እራሱን ከማጥፋት በቀር ምንም አይጠቅመውም። ከጥቂት እሑዶች በፊት **ዲቃላ ሐይማኖት**—የሚለውን ስብከት ሰብኬ ነበር። ይህም እውነት ነው። አንድን ነገር ስታዳቅሉት፡ ከዚያ በኋላ... አለቀለት! መጨረሻው ያ ነው፡ ከእንግዲህ ወደ ኋላ አይመለስም። በቅሎ እራሱን በማራባት በፍፁም ሌላ በቅሎ ሊኖረው አይችልም፡ ምክንያቱም—በቅሎ ነው፡ ድቅል ነውና። ንጹሕ በቆሎ፡ በጥሩ ከተዳቀለ በቆሎ ንጹሕ በቆሎ ማሳደግ አትችሉም። አይቻለውምም... ሊበቅል ይችላል፡ ይሁን—እንጂ፡ አይ፡ በጭራሽ አይጠቅምም። አይቻላችሁም። የተዳቀለ ነገር ሁሉ አይጠቅምም።

34 ዲቃላ ሀይማኖትም አይጠቅምም! እግዚአብሔር በተናገረው ላይ አንድ ነገር መጨመር ከሞከራችሁ፡ ወይም እግዚአብሔር እንድታደርጉት የማይፈልገውን ነገር ስታደርጉ፡ ይህ ዲቃላ ሐይማኖት ነው። ቆንጆ ሊመስል ይችላል። አቤት፡ የተዳቀለ በቆሎ የተፈጥሮውን በቆሎ ያሰንቃል። አንድ በቅሎ ስራ ሲሰራ ሁለት ፈረሶችን ያሰንቃል። ቢሆንም፡ ያ... አይሠራም፡ ወንድሜ፡ የዳንነው በጸጋ ነው። “የዳንነው በሥራ ሳይሆን፡ በጸጋ ነው።” ስለዚህ ያ... እነዚህ አስተያየቶች እንደማያሰጨንቋችሁ ተስፋ አደርጋለሁ... አሁንም—እየተሳቀቃችሁ እንዳላችሁ፡ እኔ—እዚሁ ሆኜ ይታወቀኛል። አያችሁ? ምክንያቱም እዚህ ውስጥ ፕሬስባይቴሪያን፡ ሜቶዲስት እና ሁሉም ዓይነቶች አሉ። ያንን እናውቃለን። ስለዚህ እኔም—ይሰማኛል። እና ለተወሰነ ጊዜ እራሳችሁን ዘና ለማድረግ፡ ያንን ከላያችሁ፡ እንዲህ ማራገፍ አለባችሁ።

35 አሁን አዳምጡ። የተዳቀለ ነገር ሁሉ ጥቅም የለውም። እግዚአብሔር እንደሰራው፡ ኦሪጂናሉን ነገሩን ስታገኙት፡ እውነተኛ የሆነ ነገር ይኖራችኋል።

36 እንግዲህ፡ ይህች የእስራኤል ቤተ ክርስቲያን፡ ሲያልፉ፡ እግዚአብሔር መግቦአቸዋል፡ ተንከባክቦአቸውም ነበር፡ ሁሉንም ነገር አደረገላቸው። በመጨረሻ ግን ወደ ፍልስጥኤማውያን፡ ወደ አሞራውያን፡ እና ወደ... ተለያዩ ወደ ሌሎች ተመለከቱ፡ እንዲህም አሉ፡ “እኛም ንጉስ ይንገስብን! እነርሱ በእኛ ዘንድ የሌለ ነገር አላቸውና።”

37 ዛሬም ህዝቡ የሚያደርገው ይህን ተመሳሳይ ነገር ነው። ከእነዚህ እህቶቻችን፡ አንዷ፡ ቴሌቪዥን ውስጥ ግሎሪያ ሰዋንሰንን፡ ወይም ሌሎች ማናቸውን ካየች... የተለየ አይነት ቀሚስ የለበሱ አንዳንድ ሴቶችን ስታያቸው፡ ያንን ነገር እስክታገኘው ድረስ እረፍት ያሳጣታል። አያችሁ? አንዳንድ የፒያሳ ሴቶችን አይታችሁ፡ “አቤት፡ ያምርባታል አይደል? ” እሷ ስለምትለብሰው አንቺ ምን ጨነቀሽ? ሰዎች’ኮ፡ እንዲህ ናቸው፡ እኔ እላችኋለሁ፡ አንዱ ሌላውን የሚያሰመስልበት—የማስመሰል ዘመን ነው። ተመልከቷቸው... አሁን ብዙ ኤልቪስ ፕረስሊዎች አሉ፡ እኔ—እላችኋለሁ፡ ልትቆጣጠሯቸው አትችሉም፡ ምክንያቱ እሱ በዚ ጊዜ በሰጋ ማስመሰል-... እጅግ አነጋፋ ሆኗል!

38 በሐይማኖት ውስጥ ያለው ነገርም ተመሳሳይ ነው። የ... ማርቲን ሉተርን ታሪክ እያነበብኩ ነበር፡ እና የታሪክ ምሁራን የሆናችሁ ሁላችሁ ታውቁታላችሁ። ሉተር የካቶሊክን ቤተክርስቲያን መቃወሙ እና በዚያም መጽናቱ ሚስጥራዊ

ነገር አይደለም፡ ነገር ግን ትልቁ ሚስጢር፡ የእርሱን ሪቫይቫል ተከትሎ የመጣውን ጭንቅላቱን በእጁ የሚያስይዝ አክራሪነት ቢኖርም አሁንም በቃሉ ላይ መጽናቱ ነበር። ተአምሩ ያ ነው፡ እግዚአብሔር በንጽሕና እና በቅንነት እንዴት እንደጠበቀው።

39 አሁንም፡ ወደዚህ ወደ ሳሙኤል መጡና። "እንዲህ እና-... እንዲያ አድርግልን—ወይም ንጉስ አንግስልን፡" አሉት። ጌታም ልክ የእነዚህ የድርጅቶችን አሳብ እንዳልተቀበላቸው ሁሉ፡ አሳባቸውን እንዳልተቀበለ ተናግሮታል።

40 ያንን እንዳልተቀበለው ሁሉ ድርጅቶችንም አይቀበልም። እሱ ድርጅትን እንጂ፡ ብልቶችን አይቃወምም። ብልቶች'ማ፡ ሊኖሩን ያስፈልጋል። ተቋማት ግን አያስፈልጉንም፡ ምክንያቱ መስመር ስለሚያስምሩ ነው፡ "እኛ **እንዲህ-እና-እንዲያ** ነን።" ክርስትያን ነህ? "እኔ ሜቶዲስት ነኝ።" ክርስትያን ነሽ? "እኔ ባፕቲስት ነኝ።" ይህ ማለት በአስማ ጉሮኖ እንዳለች አሳማ በዘለለ ሌላ ትርጉም የለውም። ከዚህ ጋር በምንም አይገናኝም፡ በጭራሽ። ክርስትያን!

41 አንድ ቀን ምሽት ላይ አንዲት ልጃገረድ መድረኩ ላይ፡ "ክርስቲያን ነሽ" በማለት ተየቅኳት?

"ታዲያስ፡ ይህን እንድታውቅ ልንገርህ፡ በየምሽቱ ሻማ አበራለሁ፡" አለችኝ። ከክርስትና ጋር ምንም ግንኙነት የለውም!

42 ሌላ ሰው ደግሞ፡ "እንዴ፡ እኔ'ኮ አሜሪካዊ ነኝ። በትክክል!" እንዴ፣ ያ ከዚህ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡ በጭራሽ። የሌላ መንግሥት ዜጎች ስለሆናችሁ ክርስቲያኖች ሆናችኋል። ትክክል ነው። እናንተም በሌላኛው መንግስት፡ ከላይ—ናችሁ።

43 አሁን፡ ሳሙኤል ምን አደረገ? እግዚአብሔር እዚህ ያደረገው ተመሳሳይ ነገር አደረገ። ሳሙኤልም እስራኤልን በአንድነት ጠርቶ፡ እንዲህ አላቸው፡ "አሁን አዳምጡኝ። አንድ ነገር ልጠይቃችሁ። እውነት ያልሆነ ነገር የነገርኳችሁ አንድ ጊዜ አለን? " አላቸው፡ "እኔ—በእናንተ መካከል የእግዚአብሔር ነቢይ ነኝ። አንድ ቀን በጌታ ስም የነገርኳችሁ ሳይፈጸም የቀረ አንድ ነገር ካለ ንገሩኝ።" ሳሙኤል የተናገራቸው ይህ ነበር። "እግዚአብሔርስ አልመገባችሁምን አልተንከባከባችሁምን እነዚህን ሁሉ ነገሮች አላደረገላችሁምን? " አላቸው፡ "እንደሌሎች መንግስታት ለመምሰል በመሞከር ኃጢአት እየሠራችሁ ነው፡" አላቸው።

"ኡህ... " አሉ።

44 እንዲህም አላቸው፡ "እስኪ ልጠይቃችሁ። ገንዘባችሁን ወስጃለሁን? መባ ለምኜአችሁ አውቃለሁን? ወይስ በጌታ ስም ነግሬአችሁ ሳይፈጸም የቀረ አንድ ነገር አለን? "

እነርሱም መለሱለት፡ "አይ። ገንዘባችንን በጭራሽ አልወሰድክም፡ እውነት ነው። በጌታ ስም ነግረኸን ሳይፈጸም የቀረ አንዳች ነገር አልነበረም።"

"እንግዲያውስ ሰሙኝ! እንደ ሌሎቹ ለመምሰል በመሞከራችሁ ኃጢአት እየሰራችሁ ነው፡" አላቸው። እነርሱ ግን ምንም ይሁን ንጉስ ፈለጉ! ትክክል ይሁን ስህተት ምንም ይሁን ምን፡ ሃሳባቸውን ለማስፈጸም—ፈልገው ነበር።

45 ቤተክርስቲያን በኤፌሶን ያደረገችው ተመሳሳይ ነገር ይህ ነበር፡ የኒቆላውያንን ትምህርት ወሰዱ። ይህን ባደረጉ ጊዜም፡ አረማዊነትን እና ክርስትናን በአንድነት እንዲቀይጡ ገፋፉቸው ይህም የሺ አምስት መቶ ዓመታት የጨለማ ዘመን አስከተለ። ሉተር ባወጣቸው ጊዜም፡ (ሁለተኛው ዙር) ሉተራውያን በኤፌሶን ያደረጉትን ተመሳሳይ ነገር አላደረጉም! በትክክል።

46 አሁን፡ ካስተዋላችሁ፡ የመቅረዙ አቀማመጥ ልክ **እንደሌሎቹ** አይደለም። **በዚህ** ከታች መንገድ ጀመሩና ወጡ። እንዲሁ፡ እሱ ከቆመበት ሰፍራ ከሌሎች ይልቅ የራቀው **እዚህ** ላይ ይሄኛው ነበር። ክርስትናም በመሰቀል ቅርጽ ከቆመበት ሲወጣ ቀስ በቀስ እየደበዘዘ ወጣ፡ በ 4ኛ ምዕራፍ ላይ የምናየው ይሆናል፡ በመሰቀሉ መልክ **እንደዚህ**። እና **ይሄኛው** ቀኝ እጁ ሲሆን፡ **ያ** ደግሞ ግራ እጁ ነበር። አሁን፡ **እዚህ** ጋር፡ እጁን **በዚህችኛው** እና **በዚያችኛው** ቤተ ክርስትያን ላይ አድርጓል። እሱ አልፋ እና ኦሜጋ ነበር፡ በርግጥም፡ ሌሎች ደብዳቤዎች ሁሉ፡ በሁለቱ መካከል የነበሩ ናቸው። በተለየ መልኩ ግን "አልፋ እና ኦሜጋ፡" ብሏል። በራሱ ላይም ቀሰተ ደመና ነበረው፡ እርሱ ቃል ኪዳኑ ነበር።

47 አሁን፡ ካስተዋላችሁ፡ የጴንጤቆስጤ ብርሃን፡ ከጀመረበት ስፍራ፡ ቀስ በቀስ ደብዝዟል። እነዚህ ሰዎች፡ እነ ኢራኔዎስ፣ እነ ፖሊካርፕ፣ እና ሌሎቹም በሙሉ ክርስትና በጠባብ መከራ አልፎ፡ ወደ ጨለማው ዘመን እስኪገባ ድረስ ምስክርነታቸውን በደማቸው አትመው አለፉ።

48 አሁን ተከታተሉኝ፡ በመምጣት የነበረው የከባዱ መከራ ሁለተኛው ገጽታ፡ በመጀመሪያው ዘመን መጠነኛ ብርሃን ነበረው፡ ብርሃኑ እየጨመረ፡ ከዚያም ብርሃኑ እየጨመረ መጣ። ወደዚህች ቀን እየተቃረበ ሲሄድ፡ እንደገና እንዴት ማብራት እንደ ጀመረ ተመልከቱ። አሁንም **በዚህች** ዘመን መጨረሻ ላይ፡ ወደ **ሎዶቅያ**፡ "ለብ ያለ" ወደ መሆን ያድጋል። አሁንም፡ ይሄውላችሁ። ለምን፡ **ይህ** ነገር ሌሎቹን ወደዚህ ካደረሳቸው፡ በጴንጤቆስጤ ላለን ሰዎች **ይሄን** ያህል መውረድ ለምን አስፈለገን?

49 መጽሐፍ ቅዱስ "አውሬው ይመጣል፡" በማለት እንደተናገረ ታውቃላችሁ። ይህም የሮማ ጵጵስና እንደሆነ እናውቃለን። ይህ በትክክል እውነት ነው። በመቀጠል ለአውሬው ምስል ይሰራሉ። ምስል ምንድነው? ዋናውን መስሎ የተሰራ ነው። ይህም የአብያተ ክርስትያናት ሕብረት ነው፡ ጴንጤቆስጤዎችም ገብተውበታል። ወደፊት የድርጅት አባል የምትሆኑበት ወይም ደጃችሁን መክፈት የማትችሉበት ጊዜ ይመጣል። እንግዲህ ይህ እውነት ካልሆነ ታያላችሁ! እስከሞት ድረስ የምንጎሰምበት ምክንያቱ ይህ ነው። አዎን፡ ወዳጄ። አትችሉም... ከዚያ በታችም፡ የቻሉትን ያህል፡ እጅግ ሊያጣብቧችሁ ይጥራሉ... የዚያን ድርጅት ምልክት እስካልያዛችሁ ድረስ መግዛት እና መሸጥ ይከለክሏችኋል። ይህ ማምጣታቸው አይቀሬ ነው።

50 ልክ ያኔ በዚያ ዘመን፡ እንዳቃጠሏቸው ይሆናል፡ እነርሱ... ሜዳው እኔም ጎብኝቼዋለሁ፡ ግላዲያተሮች የሚቀመጡበትን ያንን የጥንት ሜዳ አይቼው እንደ ሕፃን ልጅ አለቀስኩ። እና—በዚያ ያሉ ነገሮችን አይቼ፡ ብዙ ክርስቲያን ወንድሞቼ በአንበሶች እንደተበሉ—እና በዚያም በሜዳው ላይ ሴቶች እና ህጻናት፡ እና ሌሎች እንደተቦጫጨቁ ተረዳሁ። እና እኔም እንዲህ አሰብኩ፡ እነሱ

ሁሉም አምነው ከወረዱ፡ እኔስ አሁን እነሱን አሳፍራለሁን? አላደርገውም፡ ወዳጄ፡ ወንድሜ! አምላክ ሆይ፡ አንዴ ለቅዱሳን በተሰጠው እምነት እንድቆም እርዳኝ! ያች እንዲት ነገር ላይ፡ ምንም ያህል እውቅና የጎደላት ቢሆንም...

51 ሰው ሁል ጊዜ "መቼም" እንዲያ እንዲህ ማለት ይፈልጋል፡... በቅርብ ጊዜ አንድ ሰው ሲናገር... አቤት! ሰንቶች ታላላቅ አገልጋዮች መስክ ላይ የጋበዙኝ ጠርተው እንዲህ ብለውኛል፡ "ወንድም ብራንሃም፡ ያንን ካላቆምከው፡ ድርጅቶች ሁሉ ይነሱብሃል።"

52 "ለምን፡" እንዲህ እመልስላቸዋለሁ፡ "የማይቃወመኝ አንድ አለ፡ እርሱም በሰማያት ያለው ነው። እኔ የምፈልገው እርሱ ነው።" አያችሁ? በእያንዳንዱ ድርጅት ውስጥ ያሉ ሰዎችን እወዳለሁ። በእውነት። እኔ ግን ይህ ይሆናል ብየ በጌታ... በጌታ ስም ነግሬአችሁ፡ ሳይፈጸም የቀረ አንዳች ነገር አለን? አያችሁ? አንዳች ነገር ተነግሮ ሳይሆን የቀረ አለ ወይ? ገንዘብ ለምኜአችሁ አውቃለሁን? እንዲህ ከሆነ እንግዲያውስ ከድርጅቶ ራቁ! በክርስቶስ ነጻ ሆናችሁ ቆዩ፡ መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስትያን ውስጥ እና በውጭ በኩል ይንቀሳቀስ።

53 ማድረግ ያለባችሁ ብቸኛው ነገር፡ እነዚህን ሁሉ ጥቃቅን ልዩነቶች ከመካከላችሁ አርቁ። ጥቃቅን ርእዮተ ዓለሞች፡ እና ስለ ወንድሞቻችሁ የያዛችሁትን ጥቃቅን የማይጠቅሙ ስሜቶችን፡ እና የመሳሰሉ ነገሮችን፡ አራግፋችሁ አርቁ! መራራ ሥር ወደ ነፍሳችሁ እንዲገባ አትፍቀዱለት። ከፈቀዳችሁለት፡ ውስጣችሁን ይበላባችኋል። በትክክል። ፍቅርን ጠብቁ! ሰዎች ምንም ያህል ቢጠሏችሁ ግድ የለኝም፡ ምንም ቢሆን ውደዷቸው። ይህን ማድረግ ካልቻላችሁ፡ ይህ... ይቀራችኋል... ገና ናችሁ... አልታተማችሁም፡ ያልተሞላ ነገር አላችሁ። ስለዚህ መጥታችሁ፡ ወደ ኋላው ውጡና፡ በክርስቶስ ደም በደንብ ታትማችሁ ተመለሱ። እርሱም ከመራራ ስር ሁሉ ያነጻችኋል። አዎን።

54 እዩት፡ አሁንም ግን፡ እንደገና እየሞከርን ነው። የጴንጤቆስጤው በረከት በ1906 አካባቢ ላይ፡ ወርዷል። ከቲቤት የመጣ አንድ ሚስዮናዊ አገልጋይ፡ ዛሬ ማታ ከእኛ ጋር አለ፡ ከመጀመረያዎቹ አንደኛው-... ይህ የምናገረው እሱ ስላለ አይደለም፡ ወደ ቤት አልሄደም ብዬ ተሰፋ አደርጋለሁ። አሁንም እዚህ ያለ ይመስለኛል፡ ከመምጣቴ በፊት ትንሽ ሊሰብከን ነበርና። ይህ ሰው የጴንጤቆስጤ የመጀመሪያው ያስታውሰዋል። ድርጅት አልነበረም፡ ሁሉም የሚያመሳስላቸው ነገሮች ነበሩ። አቤት፡ በዚያ ውስጥ በስህተት ለመወሰድ እጅግ ቀላል ነው፡ ለባለእእምሮዎች'ማ እጅግ መልካም ይመስላቸዋል።

55 ይኸውላችሁ፡ ዳርቻ ላይ ቆመው በነበሩ ጊዜ እስራኤላውያን እውቀታቸው ጥቂት ነበረ፡ ይጮኻሉ... አሁንም፡ እናንተ "ይህ አይነቱ ኃይማኖት አዲስ ነው፡" ትላላችሁ። ለምን፡ ከሌሎቹ ይልቅ ጥንታዊው ይህ ነው። በትክክል። ዓለም ከመፈጠሩ በፊትም፡ በእልልታ እና በምስጋና እግዚአብሔርን ያከብሩ ነበርና። እግዚአብሔርም እንዲህ ብሎ፡ ኢዮብን ጠየቀው "ያኔ አንተ የት ነበርህ— የንጋት ከዋክብት አብረው ሲዘምሩ፡ የእግዚአብሔርም ልጆች በደስታ እልል ሲሉ።" ይህ የሆነው ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ነው።

56 አሁን ግን እስራኤልን ተመልከቱ፡ ተአምራትን አይተዋል። ይህም የዚያ ቀን በዓለ ሃምሳ፡ የእስራኤል፡ የመጀመሪያው በዓለ ሃምሳ ያ ነው። ከግብጽ

አውጥቷቸው ነበርና፡ እግዚአብሔርም ባረካቸው፡ ልዩ ልዩ ታላላቅ ምልክቶች እና ድንቆች ሰጣቸው፡ አዳናቸው። በዚያ በዳርቻው ቆመው የጴንጤቆስጤ ልምምድ ባገኛቸው ጊዜ... ይህን አደረጉ! አሁን አዳምጡ። ሙሴ በመንፈስ ይዘምራል፡ ማርያምም ከበሮውን እየመታች፡ ዳርቻው ላይ ትሮጣለች፡ በመንፈስ ትዘላለች፡ የእስራኤል ቆነጃጅትም፡ በመንፈስ እየዘለሉ ይከተሏት ነበር። የጴንጤቆስጤ ጉባኤ ማለት እሱ ካልሆነ፡ ሌላ አይቼ አላውቅም። ከእምነታቸው ማነስ የተነሣ—ተሰፋይቱ ምድር ከፊታቸው የአርባ አመት ርቀት ላይ ነበረች። ርቀቷ አርባ ማይልስ ገደማ ነበረች። አርባ ማይል ርቀት ለመጨረስ አርባ አመት የፈጀባቸው ምክንያት የተሳሳተ ነገር ስለመረጡ ነው። መንፈስ ቅዱስ እንዲመራቸው ከመፍቀድ ይልቅ ሕግ እንዲኖራቸው መረጡ፡ የእሳት አምድ በዚያ እያሳለፋቸው ይመራቸው ነበርና። እነሱ ግን የራሳቸው የሆነ ነገር እንዲኖራቸው ተመኙ፡ ልዩ ልዩ ካህናት፡ እና ልዩ ልዩ መኳንንት እንዲኖራቸው፡ እና መንፈስ ቅዱስ እንዲመራቸው ከመፍቀድ ይልቅ፡ የሚንጎራደዱበት ተራ ቲኦሎጂን ፈለጉ። በመንፈስ ነበሩ፡ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር አዘጋጅቶ ነበር፡ እነርሱ ግን የሚገቡበት አንዳች ነገር ተመኙ።

57 ድጋሚ እንደማዳቀል። ላሚቱን ለቀቅ አርጓት። ፈረሲቱን ለቀቅ አርጓት። ምግቡን ለቀቅ አርጉት። ሳይንስ... **በሪደርስ ዳይጀስት፡** በአንዲት አንቀጽ ውስጥ፡ እንደሚሉት፡ ምግቦችን እያዳቀሉ ከቆዩና፡ ሰዎችም ከተመገቧቸው... ለምሳሌ ዶሮዎችን፡ ምስኪን ዶሮን ክንፍ ወይም እግር የሌላት እስክትሆን ድረስ አድርሰዋታል። እና ከጣለችም፡ የምትጥለው በራሱ የሞተ ነው፡ ከአንድ አመት በላይ አይቆዩም። ቲሹአቸውም እጅግ ከመለስለሱ የተነሳ ለመብላት አይቻልም። ሰዎችም ይመገቡታል፡ ሰዎችን እያዛባቸው ይገኛል። ይህ እውነት ነው።

58 ግብረ ሰዶማዊነት በዩናይትድ ስቴትስ፡ ከአንድ አመት በፊት በአርባ በመቶ ገደማ እየጨመረ እንደሆነ፡ ታውቃላችሁ። እና ሳይንስ ሴቶች ትከሻቸው እየሰፋ ዳሌአቸው እየጠበበ እንደሚሄድ መናገራቸውን፡ ስለ ወንዶችም ትከሻቸው እየጠበበ ዳሌአቸው እየሰፋ እንደሚመጣ መናገራቸውን አውቃችኋልን? የተዛባ ዘር እየተመገባችሁ፡ የተዛባ ምግብ እየተመገባችሁ ትገኛላችሁና። ሰውነታችሁ ግን በተፈጥሮ ነገሮች እንዲበለጽግ ተደርጎ የተሰራ ነው። ይህስ ወደ ምን እያመራው ይገኛል? የወንዶች እና የሴቶችን ተፈጥሯዊ ሩካቤ እንኳን እየቀየረው፡ ሆሊውድ፡ እና መንግሥታችንም ሳይቀር፡ እና ሁሉም ነገር በመዛባት እስኪሞላ ድረስ ደርሷል። ምን እየሰራ ነው? በራሳቸው የእውቀት ዛፍ፡ ሞትን ወደ ራሳቸውን እያመጡ ነው።

59 ወደ መጀመሪያው ተመለሱ! ተፈጥሮውን ለቀቅ አርጉት። እግዚአብሔርን ለቀቅ አርጉት። ቤተክርስቲያንን በመንፈስ ቅዱስ አስቀጥሏት፡ እናንተም ልዩ ልዩ ትምህርት ካላቸው ቢሾፖች እና ጳጳሳት ራቁ። ወደ ጀመርንበት ተመለሱ። ተመለሱ። ኢየሱስ ዛሬ ማታ ይመጣል ሲባል፡ "እኔ ሜቶዲስት ነኝ፡" ትላላችሁ።

"ከመጀመሪያው እንዲህ አልነበረም!" ይላል፡

"እኔ ፕሪስባይቴሪያን ነኝ።"

“ከመጀመሪያው እንዲህ አልነበረም!” መጀመሪያ ላይ ምን ነበር? የጴንጤቆስጤ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ልምምድ ነበረ። የጀመረው በዚህ መንገድ ነው።

60 እኛ ግን፡ እዩት፡ ቀየርነው። ኦህ፡ እጅግ የተዋበ አደረግነው። አዎን። ያቺ እየዘለለች እና ዕልል እያለች፡ ከመንገድ ማዶ የጸናች፡ ሰዎች ድንጋይ የሚወረውሩባት፡ የሚሳለቁባቸው፡ ሌላም ሁሉ የሚያደርጉባት፡ የጸናች ቤተ ክርስትያን። ያቺ ውብ አይደለችም። “እኛ ግን ታላቁ ዶክሶሎጂ፡ እና የሐዋርያት የእምነት መግለጫ አለን፡ እና፡ አቤት፡ ፓስተራችን ዶክተር ፒኤች.ዲ.፡ ኤል.ኤል. ደብል ኤል.ዲ.፡ **እንዲህ-እና-እንዲያ** አለው።” ይመጡና እንዲህ ይላሉ፡ እስከነ አሰስ ገሰሳቸው፡ ጡንቻው እንደተሸማቀቀበት ሰው፡ “ኦህ-ማን፡” እንዲህ ይሄዳሉ።

61 ይቅርታ አርጉልኝ፡ ይ—ይህን ለማለት ፈልጌ አልነበረም። ይቅርታ አድርጉልኝ፡ እንደዚህ ለማለት ፈልጌ አይደለም። አያችሁ? ይህን ማለቴ አይደለም። ከእግዚአብሔር ሰው ይህ አይጠበቅም።

62 ይሁን እንጂ፡ ተመልከቱ፡ ሁሉም፡ እንደው... አእምሮየ ላይ መጣ፡ አያችሁ። ነገር ግን ቆመው ሁሉንም እንደዚ አይነት የተለያዩ ነገሮችን ተናገሯቸው፡ ከፊታቸው... ታውቃለህ፡ እንዲህ ሰትሉ፡ “አሁን፡ አይ፡ ይህን ትክክል አልተናገርክም። ‘ኦህ-ሜን።’” መልካም የሆነ፡ የእግዚአብሔር ኃይል የሚወርድበት የምትጮኹበት እና እልል የሚያሰብላችሁ፡ እግዚአብሔርንም የምታመስግኑበት ጥሩ ጊዜ የምታሳልፉበት፡ የድሮ የጴንጤቆስጤ ሰብሰባ እወዳለሁ። የመንፈሱ በሰዎች መያዙ፡ በዚህ መልኩ ነው። እኛ ግን... እንደው ከአሁን በኋላ “አሜን!” የሚልም አይሰማም፡ “አህ-ማን” ሆኗል። ሆኖም፡ እኛም የምናገኘው እዚህ ነው፡ አያችሁ። እነዚህ ድርጅቶች ግትሮች፡ ትዕቢተኞች...

63 እስኪ አሁንስ ሐዋ-... ስለዚህ የተናገሩት ትንቢት ነበርን? ትናንት ማታ የጳውሎስ ትንቢት ትዝ ይላችኋል? “ከሄድሁ በኋላ ጨካኞች ተኵላዎች እንዲገቡባችሁ፡ ጨካኞችም ተኵላዎች እንዲገቡባችሁ አውቃለሁ፡ በመካከላችሁ ካሉ ሰዎች፡ የእናንተ... በገዛ ቤተክርስትያኒቱ (እነዚያ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስትያን፡ እየመጡ ነው) ከእናንተ ከመካከላችሁ ወጥተው የራሳቸውን ደቀመዛሙርት ያስከትላሉ።” የጳውሎስ ተኵላዎች ደግሞ፡ ኒቆላውያን ሆነው፡ እግኝተናቸዋል።

64 መንፈስ እንደገና በነቢዩ አልፎ ሲናገር አድምጡ፡ “በመጨረሻው ቀን አስጨናቂ ጊዜ ይመጣል፡ ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና፡ (‘እኔ ዶክተር **እከሊት-እና-እከሌ** ነኝ፡ አሁንም፡ ሰለዚህ ነገር አንተ ለእኔ አትነግረኝም። ፕሬስባይቴሪያን መሆኔን ላስረዳህ። ሃሌ ሉያ!’ ወይም፡ ‘ጴንጤ’ኮ ነኝ።’)።” ተፈጥሮህ ከጴንጤቆስጤ ካልሆንክ፡ ይህ ምን ትርጉም አለው? እየህ፡ ዋናው ልምምዱ ነው። አዎን፡ ወዳጄ። “እኔ የአሴምብሊስ አባል ነኝ።” “እኔ የቸርች ኦፍ ጋድ አባል ነኝ።” እንግዲህ... በእግዚአብሔር ዘንድ ምን ትርጉም አለው? የመንግሥቱ አባል መሆን አለብኝ፡ አያችሁ። በትክክል።

65 አሁን፡ ይህን—ካያችሁት፡ እ... እነዚህ ሁሉ ነገሮች የ—የፈንጠዚያ ሰብሰባ ናቸው። አሁን፡ እንዲህ ይላል፡ “ከአምላክ ይልቅ ተድላን የሚወዱ፡

ጨካኞች፡ ትዕቢተኞች ይሆናሉ።” ኦህ፡ ጥሩ የቴሌቪዥን ፕሮግራም እስካለ ድረስ በእሁድ ምሽት ወደ ቤተ ክርስቲያን አይሄዱም። ኦህ፡ ማይ! ሁሌም እንዲህ ናቸው... አብያተ ክርስቲያናት ሳይቀር የኳስ ቡድኖች፡ እና የሾርባ እራት፡ እና የክሪኬት ድግሶች አሏቸው፡ እና፡ “ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ፡ ውል የሚያፈርሱ፡ ሐሰተኛ ከሳሾች፡ ቸልተኞች፡ መልካም የሆነውን የሚንቁ።” እዩት፡ **እነዚህ እነዚያን** ይንቋቸዋል። **እነዚህ እነዚያን** ይንቋቸዋል፡ ከዚያም ያንቋቿቸዋል። መልካሞችን የሚንቁ **ናቸው**።

66 ኦህ፡ “ወንድሜ፡ ኮሚኒስቶች ናቸው፡” እያልከን ነው። ኧረ፡ በፍጹም። በፍጹም፡ አይደለም።

67 “ጨካኞች፡ ትዕቢተኞች፡ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ፡ ውል የሚያፈርሱ፡ ሐሰተኛ ከሳሾች፡ የማይገዙ፡ መልካሞችን የሚንቁ፡ የአምልኮት **መልክ**... ” የተቋም ልምምድ፡ እያችሁ። “የአምልኮት መልክ አላቸው፡ ኃይሉን ግን ክደዋል።”

68 በዚህ ዘመን ምን ትሆናላችሁ? አይታችኋል፡ “የአምልኮት መልክ ያላቸው።” በእሁድ፡ ፈሪሃ እግዚአብሔር እንዳላችሁ ቤተ ክርስቲያን ትሄዳላችሁ፡ እሁድ ከሰአት በኋላ ቁምጣ ለብሳችሁ፡ ኧርተልሰ 92 መጠጥ ይዛችሁ ጓሮውን ታጭዳላችሁ። እንደው፡ ፓስተሩም ወደ ውጭ ወጥቶ ሲጋራ አጭሶ ይመለሳል። “የአምልኮት መልክ አላቸው!”

69 “እየህ፡ ፓስተር፡ እዚያ ባለው ቤተ ክርስትያን፡ በቀደም አንዲት ሴት ከዚህ ተፈውሳለች ብለውኛል-... ”

“እምም። እምም። ከንቱነት ነው! የተአምራት ዘመን አልፏል።”

70 “ይኸውልህ፡ ሰምተሃል እንዴ? በ—በ—በቀደም ማታ ወደ አንድ ቤተ ክርስትያን ገብቼ፡ ያቺ ማዶ ላይ ያለችው ትንሿ ተልዕኮ፡ እናም አንድ ሰው ተነሣና፡ የሆነ ነገር ተናገረ፡ ጂብ-... ”

“ኦህ፡ የኔ ማር፡ እንደ እነዚያ ካሉት ጋር አትግጠሚ። እብድ ውሾች ናቸው። ወዮ! ከነሱ ጋር አትበጂ። ያ’ኮ የሆሊ-ሮለሮች ነው። በጭራሽ አታስቢው... ”

71 “የአምልኮት መልክ አላችሁ ኃይሉንም ክደዋል፡ ከእነዚያም ራቅ። ከቤት ወደ ቤት እየሄዱ በልዩ ልዩ ምኞትም የተማረኩ ሰነፎችን ሴቶች የሚመሩ ናቸውና፡ እውነትን ወደ መማር ወይም ወደ ማወቅ ፈጽሞ መምጣት አይችሉም።” ይህ በትክክል እውነት ነው። ይኸው እንግዲህ፡ የሴቶች መረዳጃ ዕድር፡ **ይህን፡ ያንን** ዕድር። ምስኪኗ ቤተክርስቲያን ከእንግዲህ ወንጌልን እንኳን መሰበክ እስከማትችል ድረስ ብዙ ዕድሮች አሏት። ፓስተሩ ከሃያ ደቂቃ በላይ አይሰጠውም፡ በእነዚያም ስለ ሌላ ነገር ያወራል። እያችሁ፡ እንዲህ ካላደረጉ፡ የዲያቆን ቦርድ ይጠይቃቸዋል። አዎን፡ ወዳጄ።

72 ወንድም፡ ሆይ፡ ዛሬ ዛሬ ጥሩ ፓስተር ምን ማድረግ አለበት? መጽናት ባለበት ነገር የተቻለውን ሁሉ በማድረግ ቅርንጫፎቹን ቆርጦ በሚገባ ቦታቸው ማስያዝ፡ ስብርባሪዎቹንም በሚገባ ቦታቸውን በማስያዝ፡ ማስወገድ አለበት። ይኸው ነው። አዎን፡ ወዳጄ። ትክክል ነው። አንዳቸውም አት—አትለፋቸው፡ ቃሉን ሰበከው ከቃሉ ጋር ተጣበቅ፡ በደንብ ቀጥቅጥ። እስር ቤት ከጣሉህ እስር ቤት ውስጥ ሰበከው። ሌላ ቦታ ከወሰዱህ፡ በሄድክበት ቦታ ሁሉ ሰበከው፡

ዝም ብለህ፡ ሰብከትህን ቀጥል። ትክክል ነው። እና አሁን፡ የሆነው ነገር ያ ነው። አያችሁ፡ እያደበዘዙት ነው።

73 አሁን ወደ ሰምርኔስ ዘመን—እየመጣን ነው። 8ኛው ቁጥር:-

> **... በሰምርኔስም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፡ ሞቶ የነበረው ሕያውም የሆነው፡ ፊተኛውና መጨረሻው እንዲህ ይላል፡**

74 ራሱን ከቤተ ክርስቲያን ዘመን ጋር ባስተዋወቀ ቁጥር፡ የአምላክነቱን ነገር ሲያወጣ ልብ እንድትሉ እፈልጋለሁ። ከቤተክርስቲያን ጋር ለማስተዋወቅ የሚሞክረው የመጀመሪያው ነገር ይህ ነው፡ ያም፡ አምላክነቱ ነው። አምላክ ነው! ኢራኔዎስ እና ሌሎቹ ሲከራከሩበት የነበረውን ታላቁን ጉዳይ መለስ ብላችሁ ይታያችኋል? በሶስት መንፈሳዊ ህልውና የሚኖር እግዚአብሔር፡ እና በሦስት አካላት ውስጥ የሚኖር እግዚአብሔር፡ **ይሄኛው** እግዚአብሔር ለማለት ሞከሩ። እሱም "እንደዚህ ያለ ነገር የለም! የአንድ አካል ማዕረጎች ናቸው፡ እርሱም ሁሉን ቻይ አምላክ ነው፡" ይላቸው ነበር። ትክክል ነው። እናንተም አትችሉም... እነርሱም ሁልጊዜ እንደዚያ ነበሩ። እነሆ እግዚአብሔርም ራሱ በመጀመሪያ ከአምላክነቱ—አንዱ የሆነውን እያስተዋወቀ ነው። አይታችኋል እራሱን እያስተዋወቀ ነው፡ በመጀመሪያ እዚህ ጋር፡ "የነበረውም፡ ያለውም፡ የሚመጣውም እኔ ነኝ። ሁሉን ቻይ እኔ ነኝ።" አሁን እዚህ የሚጀምረው በሰምርኔስ ዘመን ነው።

75 አሁን እሱን ሰሙት፡ "እኔ... "

> ... **ወደ ሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን መልአክ** (እሱም ኢራኔዎስ እንደ ሆነ እናምናለን።) **ፊተኛውና መጨረሻው እነዚህን ነገሮች፡ ጻፍ ይላል**፡...

አያችሁ? እራሱን ሲያስተዋውቅ፡ "አሁን፡ እኔ የዚህች ቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ እግዚአብሔር ነኝ። አራት ወይም አምስት የተለያዩ አማልክቶች አጠገቤ አልፈልግም። እኔ አ—አምላክ ነኝ። አያችሁ፡ አበቃ።"

> **... የሞተው ሕያውም የሆነው፡** (አሜን!)

76 አሁን፡ አጀማመሩ—ያ ነው። አሁንም—አሁን **ሰምርኔስ** ማለት **ማይር** ወይም ከርቤ ከሚል ቃል የመጣ ሲሆን "መራራነት፡" ማለት ነው። እና የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን—የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን፡ ማለት... የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን፡ የመጀመሪያ ፍቅራቸውን ትተዋል። ይህችኛዋ ደግሞ "መራራ ሥር" ማብቀል ጀመረች ምክንያቱ በመካከላቸው ቤተ ክርስትያኒቱ፡ ዋናዋ ቤተ ክርስቲያን፡ ትልቁ ክፍል (አብዛኞቹ፡ ሁልጊዜ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪ የነበረውን መንፈስ ቅዱስ ይቃወሙት ስለነበረ ነው፡ እነርሱ በራሳቸው፡ መግዛት ፈለጉ። የካህናት ስርዓት ማቋቋም ፈለጉ፡ በብሉይ ኪዳን እንደነበሩ ሰዎች መሰራት ፈለጉ። ካህናትን ይፈልጉ ነበር። እነርሱም... የአረማውያን አማልክት፡ ያኔ፡ የተለወጡ፡ የጁፒተር ካህናት... እና ሌላ ሌላ ነገሮች፡ የቬነስ ካህናት፡ ሌላ ሌላም ነገሮች ነበሯቸው፡ **እነዚህን** ሰዎች ለማዘጋጀት ተመሳሳይ ነገር ማሰገባት ፈ—ፈ—ፈለጉ። አያችሁ፡ ነገሩ ሁሉ ከጅምሩ አረማዊነት ነው። አረማውያን ሁሉ እነዚያን አይነት ካህናቶች እና ሌሎች ነገሮች ነበሯቸው። የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ግን፡

ለእነርሱ—እንግዳ ነው። ካህናችን፡ ሊቀ ካህናችን ክርስቶስ ነው። ሊቀ ካህናት፡ እርሱም የምንበላበት ገበታ አለን።

77 አሁን፡ ይህች ቤተ ክርስቲያን "መራራ ሥር" ማብቀል ጀመረች። እንዴት? በመንፈስ ቅዱስ መቀጠል በሚፈልጉት ላይ መራራ ነበር። ፍቅር ደብዝዞ ስለ ነበረ፡ ከመነፈስ ቅዱስ አመራር በመራቅ ወደ ሃይማኖት ተቋማት እና፡ ወደ እምነት መግለጫ ለመዘፈቅ እየሞካከሩ ነበር። አሰቡት! ም—ም—ምሬት በውስጣቸው የነበረው ለዚህ ነው። እሺ።

78 አሁን፡ የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን፡ ይህ… ምሬት ወደ ውስጥዋ ዘልቆ መግባት ጀመረ። ሁለተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን፡ በስሱ ገባ። እናም፡ በስተመጨረሻ፡ "የተሻለች ቤተ ክርስቲያን ሰርተናል" ብለው እያሰቡ ስለነበረ፡ በደንብ ዘልቆ ገባባት። እዚህ ጋር ታላቁ የሮማ ህዝብ ሊገባበት የሚችል፡ አንድ የተከበረ ነገር ነበራቸው። ለምን? ጳጳስ ነበራቸው—ታላላቅ ሰዎች—ነበሯቸው፡ ካርዲናሎች፡ እና የመሳሰሉት ነበሯቸው። አለባበሳቸው ያማረ። ያኔ ከነበራቸው ከጨኸት እና ከሌላው ሁሉ ርቀዋል፡ በጣም ፀጥ ያለ ሆነ። መሞታቸውን ያሳያል። ኧህ-ህም። ኧህ-ህም። እየሞቱ ነበር። ስለዚህም ክብር አገኙና የተሻለ አካል ሠሩ። እዚህ ላይ የመጀመሪያው ነገር፡ ነገሩን በሙሉ በአንድ ትልቅ የክሃናት ሰርዓት የሐይማኖት ተቋም ውስጥ የተካተተ ነው፡ በሮማዊት አለም አቀፍ ቤተ ክርስትያን፡ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በጨለማው ዘመን። እንግዲህ፡ ያኔ፡ የተከበሩ ሰዎች ነበሯቸው፡ መደብም ነበራቸው።

79 አቤት፡ በየመንገዱ ይቅበዘበዙበት ከነበረው ጊዜ በእጅጉ የበለጠ ሆነላቸው፡ "የበግ እና የፍየል ቆዳ ለብሰው ዞሩ፡ ተቸገሩ፡ እና በመጋዝ ተሰነጠቁ፡ እና—እና መሳቂያ፡ እና መሳለቂያ ሆኑ፡" ይላል ጳውሎስ በዕብራውያን ምዕራፍ 11 ላይ እንደተናገረው።

80 እነዚያ፡ ይህች ታላቅ፡ ባለ ድንቅ፡ የተጣራ-መኅናጸፊያ ቤተ ክርስትያን፡ እስከነ የውስጥ ልብሱ የለበሱ፡ እንዲሁም—እንደዚያ የሚለብሱት ሌሎች ነገሮች ለብሰዋል። እርግጥ ነው፡ የተከበረ ይመስላል፡ "አባታችን፡ የተከበሩ፡ ዶክተር እከሌ፡ አባ **እከሌ-እና-እከሌ**።" ኦህ፡ ማይ! አንድ እውነተኛ የሆነ "አለቃ፡" ይሾማሉ።

81 ይሁን እንጂ፡ እንደምታዩት፡ የተዳቀለ ነበረ። ዲቃላ! እያችሁ፡ በውስጡ ምንም አይነት ህይወት የለውም። እና ከእንግዲህ መመለስ አይችሉም፡ ለዚህም ነው የማይነሱት። የሉተራን መነቃቃት እንደገና አልተነሳም። የዌስሊ መነቃቃት እንደገና አልተነሳም። የናዝሪን መነቃቃት እንደገና አልተነሳም። የጴንጤቆስጤ መነቃቃት እንደገና አይነሳም። ለምን? ስለ ገደላችሁት። መንፈስ ቅዱስ መንገድ እንዲኖረው በመከልከል፡ ከዓለም ጋር፡ ከኒቆላውያን ሐሳብ ጋር አዳቀላችሁት። ትክክል። ቤተ ክርስቲያንን ካዳቀላችኋት፡ እንደገና የራሷ ፍሬ ማፍራት አትችልም። በተራባችሁ ቁጥር፡ ብዙ ሜቶዲስቶች ትወልዳላችሁ፡ ባፕቲስቶችን ባራባችሁ ቁጥር፡ ብዙ ባፕቲስቶች ትወልዳላችሁ፡ ካቶሊክ በተራባ ቁጥር፡ ብዙ ካቶሊኮች ይሆናሉ፡ በላጣችሁት ቁጥር ሌላ ልጣጭ ብቻ ታገኛላችሁ። አንድ ነገር ልንገራችሁ፡ መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ ግን፡ **አዲስ** ልደት እና **አዲስ** ሕይወት ያመጣል፡ ይህም መለወጥ ነው። የመንፈስ ጥምቀት፡

ቤተክርስቲያንን እንደገና ወደ ራሱ ይመልሳታል፣ ህይወትን ወደ ውስጧ ይመልሳል።

82 የተዳቀለ በቆሎ በውስጡ ሕይወት የለውም። ምን አይነት ህይወት ነው፣ ከውስጥ የተሟጠጠ። አሁን፣ ያንን በዚያ በጨለማው ዘመን የምናገኘው፣ “የቀረህ ትንሽ ነገር፣ አጽና፣” ብሏል። ጨርሰው ጨምቀው አውጥተውት ነበር። አሁን፣ እራሱን ግን እንደገና እያባዛም። አሁን፣ የ…

83 የኢየሱስ ክርስቶስ አካል ግን—ድርጅት አይደለም። የኢየሱስ ክርስቶስ አካል መንፈሳዊ አካል ነው፣ ይህ አካል… በአንድ መንግስት ማለት በመንፈሳዊ መንግስት ውስጥ የሚገኝ ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ በምድር የተመሰረተ ራሱ የዚህ መንግስት ንጉስ፣ በዚህ መንግስት ጉዞ ለሚያደርጉ ሁሉ መስዋዕት የሚያቀርብ ሊቀ ካህን ጭምር ነው። እርሱ በዚህ መንግስት እውነትን የሚሰብክ እና የእግዚአብሔርን ብርሃን የሚያመጣ ነቢይ ነው (ቃል ነው)፣ እንዲሁም በዚህ መንግስት ውስጥ እርሱ ነብይ፣ ካህን፣ እና ንጉስ፣ ነው። እና ወደዚህ መንግሥት እንዴት እንገባለን? በሐይማኖት ተቋም ነውን? በደብዳቤ ነውን? እጅ-በመጨባበጥ ነውን? አይደለም “እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንሆን ዘንድ ተጠመቅን” እርሱም የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈሳዊ አካል ነው፣ እኛም በዚያ የተጠመቅን ሁላችንም፣ በውኃ አይደለም፣ በመርጨትም አይደለም፣ በማፍሰስም አይደለም፣ በማንኛውም የውኃ ጥምቀትም አይደለም፣ አንደኛ ቆሮንቶስ 12 ግን፣ “በአንድ መንፈስ፣ በመንፈስ ቅዱስ፣ ሁላችንም አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል።” አዎን፣ በአንዱ መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ፣ ወደዚህ አካል ተጠምቀናል፣ እንግዲያውስ ከክርስቶስ በቀር የማንም አይደለንም። የክርስቶስ ናችሁ። የተገነባው መንፈሳዊ የእግዚአብሔር መንግስት ነው፣ እኛም በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ወደዚያ እንገባለን። ይህም ደስ ይለኛል! እህም!

ሰዎች በሁሉም ስፍራ፣
ልባቸው የእሳት ነበልባል ሆኗል
በበዓለ ሃምሳ በወረደው እሳት ተነክተዋል፣
ይህም ይቀድሳቸዋል ያነጻቸዋል፣
እነሆ፣ አሁን በልቤ ውስጥ እየነደደ ነው፣
አቤቱ፣ ክብር ለስሙ ይሁን!
አንዱ ነኝ ማለቴ ደስተኛ ነኝ።

አንዱ ነኝ፣ እኔም አንዱ ነኝ፣
አንዱ ነኝ ማለቴ ደስተኛ ነኝ፣ (ሃሌ ሉያ!)
አንዱ ነኝ፣ አንዱ ነኝ፣
አንዱ ነኝ ማለቴ ደስተኛ ነኝ።

ያልተማሩ ቢሆኑም በዚህች ዓለም፣ (ዲ.ዲ.ዲ. ፒኤች.ዲ. አያችሁ።)… ያልተማሩ ቢሆኑም፣
የሚያውቃቸው ማንም ባይኖር፣
መንፈስ ቅዱስ ተሞልተዋል፣
ጠምቀው በኢየሱስ ስም፣

ለቀረበም፡ ለራቀውም ይነግራሉ፡
ኃይሉ አሁንም ያው ነው ብለው፡
አንዱ ነኝ ማለቴ ደስተኛ ነኝ።

ደስ አይላችሁም? አዎን፡ ወዳጄ። እናንተም አንዱ በመሆናችሁ። በቃ።

84 ያኔ በሜምፊስ በኩል ወደ ታች እየተራመድኩ ሲሄድ፡ ያቺ ምስኪኗ፡ ጥቁሯ እመቤት ራሷን እንዲህ አሰደግፋ ትዝ ትለኛለች። "እንደምን አደርክ፡ የእግዚአብሔር ባርያ፡" አለችኝ።

"አገልጋይ መሆኔን እንዴት አወቅሽ? " አልኳት፡

"ጌታ እንደነገረኝ፡ 'በዚህ ጎዳና በኩል ሻንጣ የያዘ፡ ክሬም ኮፍያ ያጠለቀ ባርያው፡ እንደሚመጣ ነግሮኛል፡'" አለችኝ። "መምጣትህን ሳይ አንተ እርሱ እንደሆንክ አወቅኩህ፡" አለችኝ። አያችሁ? ኦህ፡ እሷም አንዷ ነበረች። ትክክል ነው! አቤት፡ እግዚአብሔር እንዴት መልካም ነው!

85 አሁን አንድ ነገር አምናለሁ… [ወንድም ብራንሃም የተሰጠውን ማስታወሻ አነበበ—አርታዒ።] "እሁድ ማታ የ—የጸለይክላት፡ የቤድፎርዷ፡ ትንሿ ልጅ፡ አሁን እርፋለች። አይሆንም… እባካችሁ ጸሎት አድርጉ።" የጸለይንላት ትንሿ ልጅ… ከቤድፎርድ ለመጣችው ህጻን ልጅ፡ እዚህ ጸልየውላት ነበር፡ "አሁን—እርፋለች፡" ብለዋል። ጸሎት እናድርግ።

86 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ በሆነ መንገድ፡ ጌታ ሆይ፡ ጸሎታችንን ለዚያ ልጅ እንዲደርስላት፡ እጸልያለሁ። እግዚአብሔር አባታችን ሆይ፡ ህጻኗን ለአንተ አደራ ሰጠን። ስለ ህጻኗ እየጸለዩ እና ሲያስጸልዩላት እዚህ የነበሩ ሰዎች እናስባቸዋለን። እግዚአብሔር አባት ሆይ፡ ዘገባው—እውን እንዳይሆን ይህን እጠይቃለሁ፡ አባት ሆይ፡ እኛ አናውቅም፡ ነገር ግን ምህረትን እንድትሰጥ እና ብርታትን እንድትሰጣት ህጻኗም እንድትነሣ እና ለእግዚአብሔር ክብር እንድትኖር እጸልያለሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንጠይቃለን። ኣሜን። ጌታ ኢየሱስ በረከቱን ይጨምር።

87 አሁን፡ ቤተ ክርስቲያን። አሁን፡ የቤተክርስቲያን ስም ከተፈጥሮ ባህሪ ጋር የተያያዘ ነው። **ሰምርኔስ** ትርጉሙ "መራራ" ማለት እንደሆነ አስተውላችኋል? እና እያንዳንዱን ቤተክርሰትያን አሁን አስተውሉ፡ የቤተክርስቲያን ስም ከቤተክርስቲያኗ ባህሪ ጋር የተያያዘ ነው። አንድ ነገር ማለት እችላለሁ፡ ግን ባልለው ይሻለኛል፡ ምክንያቱም በሌላ መንገድ ትረዱኛላችሁ። አያችሁ?

88 ስማችሁም፡ ያው ነው። ላታውቁት ትችላላችሁ፡ ሆኖም እንዲሁ ነው። ኦህ፡ አዎን። "ኒውሞሮሎጂ ነው፡" ትሉኝ ይሆናል። በጭራሽ፡ አይደለም። **ያዕቆብ** በተወለደ ጊዜ ስሙን ያዕቆብ ብለው ጠሩት ትርጉሙም "አታላይ ነው፡" ነገር ግን ከመልአኩ ጋር ከታገለ በኋላ፡ እግዚአብሔር ስሙን **እስራኤል** ብሎ ለወጠው፡ "ልዑል" ማለት ነው። ልክ ነው? ሳውል "የጠርሴሱ ሳውል" ተባለ፡ ትንሹ ወዳጅ፡ ወደ ኢየሱስ በመጣ ጊዜ፡ ግን፡ "ጳውሎስ" ተባለ። የስምዖን ስም "ስምዖን" ነበር፡ ወደ ኢየሱስ በመጣ ጊዜ ግን፡ **ጴጥሮስ** ተባለ፡ "ትንሿ ድንጋይ።" ኦህ፡ አዎን፡ ወዳጄ። ስማችሁ… ከማንነታችሁ ጋር ይዛመዳል… በባህሪያችሁ ላይ ተጽእኖ አለው።

89 ይህች ቤተ ክርስቲያንም እየሞተች ስለነበር ሰምርኔስ ተብላለች። **ሰምርኔስ** "መራራ" ማለት ነው። በሌላ አነጋገር፡ መራራ ሥር ወጥቶ እያነቀው

ነበር፡ ወደ ከርቤ ወደመሆን ጎዳና ላይ ነበር ማለት ነው። ሬሳን የሚገነዙበት ይህ ነውና፡ ከርቤ፡ እያችሁ። ከርቤ፡ እና ዕጣን፡ እንደ ቅባት ነበር። የከርቤ ጥቅም—አስከሬኑን ከገነዙ በኋላ ወዘተ፡ ለመቀባት ያገለግል ነበር። ከሞት ጋር ተያይዞ፡ ቤተክርስቲያን እየሞተች ነበር።

90 እና፡ ኦህ፡ ዛሬስ፡ ወዳጆች ሆይ፡ ከጥቂት አመታት በፊት ህይወት የነበረው ታላቁን የጴንጤቆስጤ እንቅስቃሴ፡ አይታያችሁምን፡ አሁን በከርቤ መቀባቱ አይታያችሁም ወይ? እያችሁ? **በዚህች** ቤተ ክርስቲያን የነበረ ያው ቅባት ተዘርግፎ ወርዶ **ይህችኛዋ** ቀብቷል፡ የቅዱሳንን፡ ነጭ ልብሰ አውልቀው፡ ወደ ካህናት ሰርዓት ብቱቶ እየተመለሱ ስለሆኑ ሞት ላይ ናቸው። በዚያ ጸንተው የነበሩ ታናሽ መንጋ፡ ትክከለኛ መንፈስ ቅዱስ የነበራቸው፡ በልሳን የሚናገሩ፡ እግዚአብሔርን ገለጹ። እና፡ ወንድሜ፡ ሰዎቹ "እንዳች ነቀፌታ የሌላቸው፡" በጣም ቅኖች ነበሩ። ሙሉ—በሙሉ እውነተኞች፡ እና በማንኛውም ሁኔታ የምትተማመኑባቸው ነበሩ። አሁን ምን ማመን እና ማን ማመን እንዳለብን አናውቅም። እያችሁ? የሆነ ነገሮች ተከሰቷል። ነገሮች ተከሰቷል። ምንድናቸው? በመራራነት፡ ከርቤ እየተቀቡ ነው። ወደ ላይ አድጓል። እንዱ...

91 ይህ ምን አመጣው? አንድ ነገር ገባ፡ መጀመሪያ፡ ጠቅላይ ጉባኤ—ይባል የነበረውን፡ ቤተክርስትያን ተባለ። ከዚያ በኋላ አሴምብሊስ ኦፍ ጋድ ብለው ጠሩት። ከሴምብሊስ ኦፍ ጋድ ቸርች ኦፍ ጋድ ወጣች። ከቸርች ኦፍ ጋድ፡ ያኔ ማዶ ማየት ጀመሩ፡ "አንተ አሴምብሊስ ነህ፡" ተባባሉ። ሌላኛውም "አንተ ቸርች ኦፍ ጋድ ነህ፡" ማለት ጀመረ። ከዚያም በዚህ ችግር ምክንያት፡ ዩናይትድ ጴንጤቆስታል ቤተክርስትያን መጣች። ከዚያም፡ በመጀመሪያ እንደምታውቁት፡ ብርሃንን ከመቀበል እና በእሱ መንገድ ከመሄድ ይልቅ፡ በቃ፡ ብርሃንን መቀበል እስኪያቅታቸው ድረስ ራሳቸውን አደራጅተዋል።

92 አሁን፡ ጥምቀት "በአብ፣ በወልድ፣ እና በመንፈስ ቅዱስ" ከሚሆን ይልቅ "በኢየሱስ ክርስቶስ" ሰም—የሆነውን ጥምቀት ወደ አሴምብሊስ ኦፍ ጋድ ባቀረበላቸው ጊዜ፡ ቀድሞውንም መልሕቅ አድርገው ስለያዙት ይህን መለወጥ አልቻሉም። እውነት መሆኑን ግን ያውቃሉ! አንዳቸውንም በመጽሐፍ ቅዱስ ትክክል እንዳልሆነ እንዲያሳዩኝ ጠይቄአቸዋለሁ። ፍፁም እውነት ነው። ግን ምን ሊያደርጉ ይችላሉ? አይቀበሉትም። እያችሁ፡ የሐማኖታቸው መግለጫ ስለሚያፈርሰባቸው፡ አይቀበሉትም።

93 አሃዳውያኖቹስ ምን አደረጉ? ተቀብለውት ወደ ፊት ከመገሰገስ ይልቅ፡ ግትሮች ሆኑ፡ "እግዚአብሔር ለዘላለም ይባረክ! ብርሃኑ ከእኛ ጋር ነው፡ እናንተ ጋር የለም። እኛ እንለያለን... " ምን አደረጉት? አደራጅተውታል። እግዚአብሔርን ማደራጀት አትችሉም። እግዚአብሔር ውሱን ቅርጽ የለውም ይላል መጽሐፍ። የለውም፡ ሰለ እግዚአብሔር የተቀረ ቅርጽ ነገር የለም።

94 አሁን፡ እ—እ—እውነተኛው ቤተክርስትያን የእኛ ነው በማለት፡ አሴምብሊዎች እሱን አደራጅተው የራሳቸውን ለማድረግ ሞክረዋል። ከዚያም አኃዳውያን ተነሡ፡ እነዚህም የራሳቸውን ማደራጀት ሞከሩ፡ እነርሱም "የበለጠ ብርሃን ነበራቸው።" ታዲያ ምን አደረጉ? በሰግብግብነት እና በራስ ወዳድነት፡ ነገሩን ይዘው እያፋፋሙት ወጡ። በጨውና በመልካም

ጣዕም ነገሩን በማካፈል ፈንታ፡ ከሱ ጋር ምንም ጉዳይ የለንም በማለት፡ ሌላውን ማስወገድ ሞከሩ። ያመጣውም ይህ ነው። ከዚያም፡ ጠራርጎ ገባ። ይኸውላችሁ በመጀመሪያ የሆነው ነገር፡ ሌሎች ተነሡና፡ **ይህንን** ያዙ፡ በዚህም ተለያዩ። አንደኛው "የሚመጣው በነጭ ፈረስ ነው፡" ይላል። ሌላውም ይላል፡ "የሚመጣው በነጭ ደመና ነው። እግዚአብሄር ይባረክ፡ የራሴ ድርጅት እከፍታለሁ።" ስራቸው ምን እንደሚያደርግ አይታችኋል? ከርቤ—ከርቤን ያስፋፋል። ምን አደረገ? ወንድማማችነትን ዘጋ።

95 በአሴምብሊስ ኦፍ ጋድ ውስጥ የሚገኙ፡ ብዙ ወንዶች፡ እና ሴቶች፡ ዛሬ ማታ፡ ይህ የእግዚአብሔር እውነት መሆኑን በማወቃቸው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ለመጠመቅ መምጣት ይፈልጋለሁ። ይህን ካደረጉ ግን ይወገዛሉ።

96 እና ብዙ የአንድ አምላክ አማኞች… እንግዲህ፡ እኔ አኃዳዊ አይደለሁም። እነርሱ በሚሉት "አኃዳዊነት" እኔ አላምንም። እነሱ **ኢየሱስ** በሚሉት መንገድ አላምንም፡ "**ኢየሱስ**"፡ ብዙ ኢየሱሶች አሉና። እሱ **ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ** ነውና። ትክክል። አሁንም፡ አላምንም… እነሱ ከሚሉት ነገር ይለያል ብዬ አምናለሁ። በኢየሱስ ስም፡ በኢየሱስ ስም የሚጠመቁት መዳን ነውና፡ ይህም "መጠመቅ (መዳን) በውኃ ስለመጠመቃችሁ ክርስቶስን ወደ እናንተ የሚያስመጣ ነው።" ይህን አላምንም። መዳን የሚመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ ደም በመንፈስ ቅዱስ በኩል እንደሆነ አምናለሁ። ትክክል ነው። ጥምቀት ለተደረገው ውስጣዊ የመዳን ስራ ውጫዊ ተግባር ብቻ ነው። አያችሁ? ስለዚህ፡ በዚያ አልስማማም። ችግርም የለውም፡ ይሁን እንጂ ሁሉም ወንድሞቼ ናቸው።

97 መጀመሪያ እንደ ባፕቲስት ሰባኪነት ስጀምር፡ እንዲህ እያሉ ይመጡ ነበር፡ "ወንድም ብራንሃም፡ ወደዚህ ና፡ እ—እ—እኛጋ ይህን ይዘናል ወደ እኛ ና።"

98 "ከሁለታችሁ ውጪ፡ በሁለታችሁ ቡድኖች መካከል እቆማለሁ፡ 'ወንድማማቾች ነን!'" አልኳቸው፡ ምንም ቢሆን አይገደኝም፡ ሰው አልስማማም ቢልም ለእኔ አያስጨንቀኝም፡ በእኔ ዘንድ አንዲት ልዩነት አይፈጥርም፡ አሁንም ወንድሜ ነው።

99 አፕል ፓይ የሚወድ ወንድም አለኝ፡ እኔ ግን ቼሪን አብልጬ እወዳለሁ፡ በዚህ ምክንያት ግን ከእርሱ ጋር የነበረኝን ህብረት አላቆምም። እሱ አፕል ፓዩን ይመገባል እኔም የራሴን ቼሪ ፓይ እመገባለሁ። የራሴ ላይ **ካፍ ስሎበርስ** እጨምርበታለሁ፡ እሱ የማይፈልግ ከሆነ፡ ቢፈልግ፡ መጨመርም ይችላል። ምን እንደሆነ… ታውቁታላችሁ? በደንብ የተመታ ነገር በላዩ ላይ ይጨምሩበታል፡ "የተመታ ክሬም ነው፡" ታውቁታላችሁ። እወደዋለሁ። አሁን እሱን ለመብላት በጣም አርጅቻለሁ፡ ያ ነው… ነገር ግን እ—እ—እኔ… የምወደው ያ ነው። ካልተመቸው፡ መብላት የለበትም። ችግር የለውም፡ የራሴን እበላለሁ። አሁንም ግን ወንድሜ ነው! ትክክል።

100 በተጨማሪም—ያንን እወዳለሁ፡ ሕብረት ማድረግ እወዳለሁ። "አይ፡ ይህ **የራሳችን** ተቋም ነው፡" እያልን፡ እንደዚህ አይነት መስመሮች ስናስምር፡ አጠገባችን ያለውን ሰው እጃችንን ዘርግተን ሰላም ማለት፡ "እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወንድሜ!" ለማለት ከተቸገርን፡ ማይ! ይህም ለሕብረት ስትጠራሩ ማለት ነው። ሰላም ካልተባባላችሁ፡ ያኔ ስምርኔስ ላይ

እንደነበረባቸው መራራነት ተጠናውቶባችኋል፡ በዚህም ምክንያት ተመሳሳይ ችግር ትፈጥራላችሁ። በጣም ጥሩ፡ ስለዚህ ስማቸው "መራራ" ነበረ።

101 ኒቆላውያኖች እስከ ጨለማው ዘመን ድረስ እነሱን መጥረግ ቀጠሉበት። የሉተር ዘመን የመጀመሪያውን የጸጋ እርከን አመጣ፡ ትንሽ ብርሃን ማንጸባረቅ ጀመረ። ከሱ በኋላም ሌላ መጣ፡ ጆን ዌስሊ ቅድስና እያለ መጣ፡ ብርሃኑን በትንሹ አደመቀው። ከዚያም በኋላ ጴንጤስጤዎች፡ የአባቶችን እምነት እንደገና በመመለስ ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ጋር መጡ። በዚያ መልኩ ማቆየት ስላልቻሉ ግን፡ ማደራጀት ጀመሩ፡ ወዲያውም እንደገና ወደ ኒቆላዊያን መመለስ ጀመሩ። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያደርጉት የተናገረው ይህ ነበርና።

102 አሁን፡ እዚህ ጋር መጠንቀቅ አለብኝ ካልሆነ ግን... ብዙ ጊዜ ይወስድብኛል። ወደ 2ኛው ቁጥር እንሂድ፡ ወይም... ወደ 8፡ 9ኛ ቁጥር ነው። እሺ፡ አሁን ስለ ስደቱ፡ 9ኛው ቁጥር፦

> **ሥራህንና፡** መከራህን፡... **ድህነትህን አውቃለሁ፡ (ነገር ግን ባለ ጠጋ ነህ)...** (ኦህ፡ ማይ!)... **እኔ...** (አሁን ከቤተክርስቲያን ጋር እየተነጋገረ ነው፡ እውነተኛይቱን ቤተክርስቲያን እንጂ፡ ሌሎቹን አይደለም፡ የኒቆላውያንን ስራዎችን ጠልተውት ነበርና።) ... **የሰይጣን ማኅበር** ናቸው **እንጂ፡ አይሁድ ሳይሆኑ አይሁድ ነን የሚሉትን፡ የሚሳደቡትን ሰድብ አውቃለሁ።**

103 በጉስቁልና-ተመትተው ነበር። እና፡ ቅሬታ ነበራቸው። የነበራቸው ሁሉ... ተወሰዶባቸው ነበርና። ትንሿን ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዲህ ሠርተው ነበርና፡ ትናንሽ ብዱኖች በመሆናቸው፡ ትልቁ ቤተክርስትያን፡ ይገፈትራቸው ነበር፡ ያስወጧቸውም ነበር። እንዲህ ተባሉ፡ "አውቃለሁ። በየማእዘኑ ላይ መሰብሰብ እንዳለባችሁ፡ በየመንገዱ፡ ወይም ባገኛችሁት ሰፍራ ሁሉ መሰብሰብ እንዳለባችሁ አውቃለሁ።" (እኔ ራሴ ያኔ ይሰበሰቡበት የነበረውን፡ ከመሬታ በታች ወርደው፡ ሰራዎቻቸውን የሚያደርጉበት ካታኮምብስ ጎብኝቼዋለሁ።) "መከራህን አውቀዋለሁ፡ ችግሮችህን አውቀዋለሁ፡ እና የመሳሰሉትን፡ ነገር ግን በእነዚያ መከራዎች ባለ ጠጎች ሆናችኋል።" ኦህ፡ ማይ! በቤተክርስቲያን ላይ ስደት በሚመጣበት ጊዜ ሁሉ፡ ያጠነክራታል። በመከራ ውስጥ፡ ሁል ጊዜ ቤተክርስቲያንን ትበረታለች። "መከራህን አውቃለሁ፡ ነገር ግን ባለጸጋ ነህ።" ለምን? "እኔን ስለያዝክ፡ ባለጸጋ ነህ። መከራዎችህ አይጎዱህም።"

104 አሁን፡ ይህን... አስተውላችኋልን? ኒቆላውያኖቹ የራሳቸው ምኩራብ ሰርተዋል። መጽሐፍ ቅዱስ እዚህ ጋር እንዲህ ይላል። በ9ኛው ቁጥር አስተውላችኋል?

> ይህም... **የሰይጣን ማኅበር ናቸው... እንጂ፡ እንዲህ አይደሉም።**

105 ኧህ-ህህ፡ እውነተኛዋ ቤተክርስቲያን ተገፍታለች። ኒቆላውያን በርትተው፡ እነዚያን... መንፈስ ቅዱስ የነበረባቸው ሰዎችን ገፍተው አስወጧቸው፡ ስለዚህ እነሱ—በፊታቸው ጥቅም አልባ ነበሩ። በእስያ የነበረችው፡ ስምርኔስ፡ እነዚህን ነገሮች ብቻ ብታውቅ ኖሮ... የሰማዕት አክሊሎች እንደሚጠብቃቸው ቢያውቁ፡ ይጨባበጡ ነበር። እያችሁ? አሁን፡ በሌላ አባባል፡ ይህ... ትንቢት በተነገረ ጊዜ እና በተላከላቸው ጊዜ፡ ያቺ ቤተ ክርስቲያንም ተቀበለችው፡ የሰማዕቱንም

አክሊል ደፍተው ሊሄዱ የሚገባቸው እነርሱ መሆናቸውን አስተውለዋል፡ ለምን፡ ተቀብለውታል... ባይሆን ግን፡ እስከ ሞት ድረስ ፍርሃት ይይዛቸው ነበር። በማንኛውም ጊዜ ጠበቁት። በዘመናቸው ግን አልመጣም። ያኔ ምናልባት አንዳንዶቹ፡ "እንግዲህ፡ አያችሁ—አያችሁ፡ እላችኋለሁ፡ ያ ነቢይ ተሳስቶ እንደነበር። ዮሃንስ ተሳስቷል፡ ም—ም... ምክንያቱ በሰምርኔስ በእኛ ዘንድ ይህ አልሆነም።" ለምን፡ ከመቶ አመታት በኋላ መሆን ነበረበት። አያችሁ? እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር ሁሉ ግን፡ መሆኑ አይቀርም።

106 እምነታችንን የምንጠልቅበት፡ በዚያ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ነው። እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ሁሉ ይጠብቃል። ምንም ቢሆን... አሁን መሆን አለበት ብለህ ታስብ ይሆናል፡ ነገር ግን ይህ እንዲሆን የእግዚአብሔር ጊዜ ላይሆን ይችላል። "ቃሌ ግን የታሰበውን ይፈጽማል እንጂ፡ ወደ እኔ በከንቱ አይመለሰም።" እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ቃሉን ያከብራል፡ በራሱ መልካም ጊዜም ይፈጽመዋል።

107 ስለዚህ እነዚህ ሰዎች፡ የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን እነሱ ነበሩ፡ በዚያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ግን በኋላ በሰምርኔስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚወጣው ገጸ ባህርያት ነበረ። እንግዲህ የሰማዕታት አክሊል የሚደፋበት፡ ብዙዎች የሚገደሉበት፡ ያኔ ነበረ።

108 አሁንም ይህን ሰናነብብ—10ኛው ቁጥር፡ እንውሰድ፡

> **መከራ ከምትቀበልባቸው** ከእነዚህ **ነገሮች** (ከሰይጣን ማኅበር) **አትፍራ፡ እነሆ፡ እንድትፈተኑ፡ ዲያብሎስ ከእናንተ... አንዳንዶቻችሁን በወኅኒ ሊያገባችሁ አለው፡ አሥር ቀንም መከራን** ትቀበላላችሁ፡ **እስከሞት ድረስ የታመንህ ሁን፡ የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ።**

109 ኦህ፡ ማይ! ስለ ሐይማኖታቸው እንዲሞቱ ጥሪ በቀረበላቸው ጊዜ—እንዳይፈሩ ተነገራቸው። አሁንም፡ እህት ውድ፡ ባለሽበት ሆነሽ፡ ይህን እንደሚያጸናሽ ተሰፋ አደርጋለሁ። እህት ውድ፡ በቀደምለት የነገረችኝ ነገር ነበር፡ አንዳንዶች ተፈውሰው ሌሎች የማይፈወሱበት ምክንያት ለምን እንደሆነ አይገባትም። አንዳንድ ጊዜ ማወቅ አለባችሁ... እግዚአብሔር ለእነዚህ ሰዎች እንዲህ ብሏቸዋል፡ "አሁን፡ ይህ አያስፈራችሁ፡ ምክንያቱም ሰይጣን ወደዚያ ሊጥላችሁ አለውና፡ ምክንያቱ ይህወደዚያ የሚያስገባችሁህ ኒቆላውያን መጥቶ ሲገፈትራችሁ፡ እኔ ራሴ ሰለ ሰራዬ እንድትሞቱ ሰለፈለግኳችሁ ነው። በዚያ ቀን ግን የሕይወትን አክሊል እሰታችኋለሁ።" ስለዚህ አት...

110 አሁን ተመልከቱ፡ እንዲህ አላቸው... አሁን፡ 10ኛውን ቁጥር ሰናነብ ካስተዋላችሁ። ደግሜ ላንብበው፡-

> **ከምትቀበለው መከራ** ምንም **አትፍራ፡ እነሆ፡ እንድትፈተኑ፡ ዲያብሎስ** ከእናንተ **አንዳንዶቻችሁን ወደ ወኅኒ ይጥላል፡ አሥር ቀንም መከራን ትቀበላላችሁ፡** አንተ **ግን ለመሞት የታመንህ ሁን**... (**እስከ** እንደሚል አስተውላችኋል? **እስከ** ሞት ድረሰ ሳይሆን፡ **ለመሞት** ነው። ገብቷችኋል? ) ... **ለመሞት የታመንህ ሁን**፡... (አያችሁ? እንዲሁም ሆኑ።)

111 አሁን እንግዲህ፡ ሰይጣን አለ... ይህን ሁሉ ሲያደርግ የነበረው ማን—ማን ነው እንዳለ አስተውላችኋል? እነኚህ፡ **የሰይጣን ማሕበርተኞች** “ኒቆላውያኖች” ናቸው። ይህን እናውቀዋለን። አይደሉም’ዴ? ያኔ እነዚህን ሰዎች መከራ ውስጥ የሚያደርስ ድርጅት፡ ያኔ እየተነሳሳ የነበረ የካህናት ሰርዓት ነበር፡ ይህም ሰዎችን ያሰቃያቸው ነበር፡ እነርሱ ግን ስለወንጌል **ለመሞትም** የታመኑ ነበሩ። በጋብቻ ሥነ ሥርዓት ላይ አስተውላችኋል፡ “ሞት እስኪለየን **ድረስ**” አይደለም፡ ነገር ግን “**ወደ** ሞት እስክንደርስ።”? አያችሁ? እንግዲህ፡ **ወደ** እና **ድረስ** የተለያዩ ናቸው። እንግዲህ፡ ስለ ክርስቶስ ለመሞትም ታማኞች ነበሩ። “ከእሱ ጋር እስከ ሞት ድረስ ሂድ። አክሊል እሰጥሃለሁና፡ አትፍራ።”

112 አሁን አሁን የሚናገሩላቸው፡ እነዚህ “አሥር ቀናት” አሥር ቅናት። ቀን በመጽሀፍ ቅዱስ ዓመትን ይወክላልና። **አሥሩም ቀናት** ዲ-ዮ-ቅ-ል-ጢ-ያ-ኖ-ሰ፡ የዲዮቅልጥያኖስ መንግሰት የመጨረሻዎቹ “አሥር አመታት” ናቸው። የዲዮቅልጥያኖስ። በመጨረሻዎቹ ዓመታት ንጉስ የነበረው፡ ዲዮቅልጥያኖስ ነበረ... እንግዲህ፡ በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ዘመን ብዙ ነገሥታት ነግሰዋል። አንደኛው፡ ኔሮ፡ እንደነበረ አምናለሁ። ይህም ዲዮቅልጥያኖስ በመጨረሻው አሥር ዓመታት የነገሠው፡ የመጨረሻው ነው፡ እና ከሁሉም የበለጠ ደም አፍሳሽ እርሱ ነበር። ዝም ብሎ ከዚህ ቡድን ር ወገነና—ክርስቲያኖችን ይገድላሉ፡ እና ይገድሏቸው ነበር፡ ያቃጥሏቸው ነበር. ሁሉም—ነገር ያደርጉባቸው ነበር፡ እና እጅግ የከፋ ደም አፋሳሽ አሰር ዓመታት ነበሩ። ዘመኑና የግዛቱ ዘመን ከ302 እስከ 312 ነበር። ይህ የሰምርኔስ ዘመን፡ በቆስጠንጢኖስ መምጣት አብቅቷል። እርሱም ማለት ቆስጠንጢኖስ፡ በ312 መጣ። አሥሩ የመከራ ቀናት እነዚያ ነበሩ። በኔሮ ተጀምሮ በዲዮቅልጥያኖስ ተጠናቀቀ። እና በኔሮ ውስጥ የጀመረው፡ ** እ.ኤ.አ** በ 64 ዓመተ ምሕረት ኔሮ ዙፋኑን በያዘ ጊዜ ነው።

113 አሁን፡ 11ኛው ቁጥር ቃል ኪዳን ነው። ከመዘጋቱ በፊት ይህንን እናገኛለን፡

> **መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን፡ ጆሮ** ያለው **ይሰማ፡ ድል የነሣው በሁለተኛው ሞት አይጐዳም።**

114 አሁን፡ የሆነ ነገር እዚህ መናገር አለብኝ፡ ይህም... ልቤ፡ ያሰበውን፡ መናገር ካልቻልኩኝ፡ እንግዲያውስ ግብዝ ነኝ። አያችሁ? በዚህ ቃል ውስጥ አንድ ነገር እንድታስተውሉ እፈልጋለሁ፡ እና እኔም እስክደርስበት ድረስ ለረጅም ጊዜ ለእኔም ትልቅ እንቆቅልሽ ከሆኑት አንዱ ይመስለኛል። አሁንም እስኪ በደንብ አስተውለን እናነበዋለን፡ አሁን። አያችሁ?

> **ጆሮ ያለው፡** (በሌላ አነጋገር “የሚሰማ ጆሮ አለው፡” አያችሁ፡ ለመንፈስ ክፍት ነው።) **መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ይሰማ፡**...

አሁን እዩት፡ ይህ ተመሳሳይ ነገር፡ ይህ ሰደት እና ሁሉም ነገር መጣ። እያንዳንዱ ክፍል በየቤተ ክርስቲያኑ እየተደራረበ ተጋጥሟል። **አብያተ ክርስቲያናት**።

> ... **መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት** እንዲህ ይላል፡ **ድል ለነሳው...** (በየትኛው ቤተ ክርስቲያን? የኤፌሶን? አዎን። በጣም ጥሩ። ሰምርኔስ? አዎን፡ በሁሉም።) ... በየአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ **ድል የነሣ በሁለተኛው ሞት አይጎዳም።**

115 በሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ምን ድል የነሣ ነው? ኒቆላውያንን ድል የነሣ፡ የዓለምን ነገር ድል የነሣ፡ እነዚህን ተቋማት ድል የነሣ፡ እነዚህን የካህናት ስርዓት ድል የነሣ፡ የዓለምን ሁሉ አሸንፎ ሸጦ፡ ክርስቶስንም የወደደ። በሁለተኛው ሞት አትጎዱም። ለምን? የዘላለም ሕይወት አግኝቷል። የዘላለም ሕይወት አይሞትምና። ኢየሱስም "ከእኔ የሚሰማ የዘላለም ሕይወት አለው፡ ለዘላለምም አይሞትም። በመጨረሻው ቀን አስነሳዋለሁ፡" አለ።

116 እንግዲህ፡ አሁን፡ እዚህጋ... አሁን ምናልባት እናንተም... ሌሎችም በዚህ ላይሰማሙ ይችላሉ፡ ነገር ግን ውሳኔ ከማድረጋችሁ በፊት በትክክል እንድታስቡ እፈልጋለሁ። አያችሁ? አሁን አንድ ነገር ልበል፦

117 የዘላለም ሲኦል አለ ብዬ የማላምንበት ምክንያት ይህ ነው። የዘላለም ሲኦል ሊኖር አይችልም። ምክንያቱም የዘላለም ሲኦል ቢኖር ኖሮ፡ ሁልጊዜ ዘለአለማዊ መሆኑ አይቀርም ነበር፡ ምክንያቱ ዘለአለማዊ... አንዲት አይነት ዘለአለማዊ ህይወት ብቻ አለች፡ እኛም የምጥረው እሷን ለማግኘት ነው። ለወትሮ እና ለዘለአለም የምትቃጠሉ ከሆናችሁ ግን፡ የሚነድ የዘላለም ህይወት ሊኖራችሁ ግድ ይሆንባችኋል፡ ያኔ የሚቃጠለውም እግዚአብሔር ይሆናል ማለት ነው። ዘላለማዊ ሲኦል ሊኖር አይችልም፡ መጽሐፍ ቅዱስም በግልፅ "ሲኦል የተዘጋጀ ነው" በማለት ይናገራልና። የተዘጋጀ ከሆነ፡ እንግዲያውስ ዘላለማዊ አይደለም። ዘላለማዊ የሆነ ሁሉ ሊዘጋጅ አይችልምና፡ ሁሌም የነበረ፡ ዘላለማዊ ነውና። መጽሐፍ ቅዱስም "ሲኦል የተዘጋጀው ለዲያብሎስና ለመላእክቱ ነው።" ሲኦል የተዘጋጀ ስለሆነ፡ ዘላለማዊ አይደለም። እና አንድ ሰው ዘላለማዊ ቅጣት ይኖረዋል ብዬ አላምንም።

118 መጽሐፍ ቅዱስ እዚህ ላይ በግልጽ፡ እንዲህ በማለት እንደሚናገር አምናለሁ፡ "ድል የነሣው በሁለተኛው ሞት አይጎዳም።" አሁን "ሞት።" **ሞት** የሚለው ቃል የመጣው ከ... ከ "መለያየት፡" ነው። አሁን፡ ከእግዚአብሔር ስንለይ፡ በኃጢአት፡ ቀድሞውንም ሞተናል፡ መጽሐፍ ቅዱስ ይላልና። ከእግዚአብሔር ተለይተናል፡ ተቆርጠናል፡ በኃጢአትና በበደላችን ሙታን ነን፡ እኛ ለእግዚአብሔር እና ለመንግስቱ ባዕድ ነን። ከዚያም እግዚአብሔርን ስንቀበል እና የዘላለም ሕይወት ሲኖረን፡ የእርሱ ልጆች እና የእርሱ አካል ነን።

119 እዚያጋ ያለው፡ ትንሹ ልጄ ዮሴፍ፡ ምንም ቢያደርግም፡ አካሌ... ነው። እሱ... እኔ ምናልባት... ላያገኝ ይችላል... እኔ ባለ ብዙ ርስት ባለጸጋ ሰው ብሆን ኖሮ፡ ምናልባትም፡ ምንም ነገር ላይወርስ ይችላል፡ ይሁን እንጂ ልጅ ነው፡ አካሌ ነው። አዎን፡ የእኔ አካል ነው። ስለዚህ፡ እኔ ራሴን መካድ እንደማልችል ሁሉ፡ እሱን መካድ አይቻለኝም። የደም ምርመራው የእኔ መሆኑን ያሳያል። አያችሁ?

120 እናንተም የደም ምርመራው የእግዚአብሔር መሆን አለመሆናችሁን ያሳያል። አያችሁ? እናንተ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና የዘላለም ሕይወት አላችሁ። ነገር ግን ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ፡ ያቺ **ነፍስ** ትለያለች። ልክ ነው? ከዚያ በኋላ አትኖርም። አሁን ተመልከቱ። መጀመሪያ ያለው ሁሉ ፍጻሜ አለው፡ ምክንያቱም መጀመሪያ ያለው ሁሉ የተፈጠረ ነውና። እግዚአብሔር ግን አልተፈጠረም፡ ሁልጊዜም አምላክ ነበር። እሱ የተፈጠረበት ሰፍራ የለም። እና የዘላለም ሕይወት ማግኘት የምንችልበት ብቸኛው መንገድ የፍጥረቱ አካል በመሆን ነው። ክብር! አቤት፡ ማየት በቻልን ኖሮ! መንፈስ ቅዱስ

ለእናንተ የሚያደርገውን አይታችኋል? በመንፈስ መልክ ያለው፡ ራሱ ፈጣሪ፡ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር አብ፡ "መንፈስ ቅዱስ" ይባላል፡ ምክንያቱ እሱ በፈጠረው ኢየሱስ በሚባለው በልጁ ሰውነት፡ በአካሉ፡ ውስጥ ስላደረ ነው፡ መሞት የነበረበትም ለዚህ ነው። እግዚአብሔር በዚህ በሰው ሥጋ አደረ፡ የደም ሕዋስ ተቆረሰ፡ ከደም ሴል የተገኘው ሕይወትም ተመልሶ መጣ።

121 በብሉይ ኪዳን የነበረው የጥንት መስዋዕት አቅራቢው ሊጠፋለት ያልቻለው ለዚህ ነው… ይዞት የመጣውን ተመሳሳይ ኩነኔ ይዞት ይመለስ ነበርና። በአዲስ ኪዳን ግን፡ ዕብራውያን ላይ፡ እንዲህ ብለዋል፦ "መስዋዕት የሚያቀርበው አንዴ ከነጻ በኋላ የኃጢአት ሕሊና የለውም።"

122 ያኔ፡ በብሉይ ኪዳን፡ ጠቦት ያመጣሉ፡ መስዋዕት የሚያቀርበውም፡ እጁን፡ በላዩ ይጭንበታል፡ ካህኑ ጉሮሮውን ይቆርጠዋል፡ የደሙ መፍሰስ ሰሜት ይሰማዋል፡ ማንቋረሩንም ይሰማል። ይሞታል፡ ትንሿ አካሉ ትዝለፈለፋለች፡ ያኔ ይሞታል። እንደዚያ መሆን የነበረበት እርሱ ራሱ እንደነበረ ያውቃል፡ ይሁን እንጂ በጉ ስፍራውን ይተካል። ካህኑ ደሙን ወሰዶ፡ በመሠዊያው ላይ ይረጨዋል—ጢሱም ወደ ላይ ይወጣል፡ መስዋዕት ለሚያቀርብ ሰው የይቅርታ ጸሎት ነው-… [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።] … እና የእንሰሳው ህይወት በሰው ላይ ተመልሶ ከሰው መንፈስ ጋር ሊጋጠም አይችልም፡ ምክንያቱ የእንሰሳት መንፈስ ነው። የእንሰሳት ህይወት እና የሰው ህይወት፡ ማቀላቀል አይቻልም። ነገር ግን… እንዲሁ ኃጢአትን ለመሥራት ተመሳሳይ ፍላጎት፡ በቀድሞ ሰሜቱ የሚመለሰው ለዚያ ነው። ዝሙት ሰርቶ የመጣ፡ መስዋዕቱን ያቀርባል፡ አእምሮው ውስጥ ተመሳሳይ ፍላጎት አዝሎ ይመለሳል። በትክክል።

123 እዚህ ግን መስዋዕት የሚያቀርብ… ኦህ፡ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ሆይ፡ ይህ መረዳት አያቅተቻሁ! መስዋዕት አቅራቢው፡ አንዴ ፈጽሞ እጆቹን በእምነት ወደ እግዚአብሔር ልጅ ከጫነ (ኦህ፡ ማይ!) ፊቱ ላይ ተተፍቶበት ፊቱ ላይ የተንጠለጠለ፡ ደሙ በፊቱ ላይ እየፈሰሰ ታዩታላችሁ፡ ህመሙ ይሰማችኋል "አምላኬ! አምላኬ! ለምን ተውኸኝ?" ኦህ፡ ወንድሜ ሆይ፡ ስለ አንተ የሞተልህ፡ አማኑኤል፡ ማን እንደሆነ ብታይ፡ በአንተ ምትክ የሞተልህ እግዚአብሔር ራሱ ነው።

124 ከዚያ ምን ይሆናል? መስዋዕት አቅራቢው፡ ያ የደም ሕዋስ በእግዚአብሔር ልጅ ውስጥ በተቆረሰ ጊዜ… ያንን የደም ሕዋስ የፈጠረው ምንድን ነው?

125 እናንተ ምንድናችሁ? ከአባታችሁህ የወጣችሁ ትንሹ ሕዋስ ናችሁ። ሴቲቱ ሄሞግሎቢን የላትም። ሴ—ሴቷ እንቁላል ብቻ ታዘጋጃለች፡ ማህጸኗ፡ ል—ል—ልጆችን ለማቀፍ ብቻ ነው። ደሙ የሚመጣው ግን ከወንዱ ነው፡ ለዚህም ነው—ልጁ የአባቱን ስም የሚወሰደው። ከዚያም፡ ሴቲቱ ግን፡ ከወንዱ ጋር ስታገባ፡ ልክ እንደ ልጆቹ፡ ሰሙን ትወሰዳለች፡ ለወንዱ ለምትወልድለት ልጆች ማሕጸን ትሆንለታለች። እንዳልኩት ግን፡ ዶሮ እንቁላል መጣል ትችላለች፡ ከወንዱ ዶሮ ጋር ካልተገናኘች ግን፡ አይፈለፈልም።

126 እኔም ያልኩት፡ ይህ ነው፡ ዛሬም ቀዝቃዞች፡ እና ተራ፡ ያረጁ አብያተ ክርስትያናት ያሉን ለዚህ ነው። በዚህ በኒቆላውያን አሳብ ይጠመዳሉ፡ ብዙ መረብ ቢኖራቸውም የበሰበሱ እንቁላሎች ብቻ ናቸው፡ ስለሆነም በጭራሽ

አይፈለፈሉም... ብዙ ነገር ብላችሁ ልትጠሯቸው ትችላላችሁ (ቢሾፖች፡ ዲያቆናት፡ እና ሌላም ሁሉ)፡ አማኞችን በሚከተሉ ምልክቶች ፈጽሞ አያምኑም፡ ምክንያቱም ከትዳር ጓደኛው፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አብረው ሆነው አያውቁም። ከእግዚአብሄር ሃይል በትዳር አጋርነት የተገናኛችሁ እንደሆነ...

127 ያ የደም ሕዋስ በቀራንዮ ላይ በተቆረሰ ጊዜ፡ እና በዚያ የነበረው ሕይወት፡ ትሁት ጀሆቫ... ኦህ፡ ሊያስገርማችሁ ይገባል!

128 ታውቃላችሁ፡ ሰዎች ሁሉ ምልክትን ይፈልጋሉ፡ አይደሉም'ዴ? ሰው ሁሉ፡ "ኦህ፡ ምልክት አሳየኝ።" አይሁድም "ምልክትን አሳየን፡" አሉት።

129 ምልክት ልሰጣችሁ። አንድ ጊዜ እግዚአብሔር ምልክት ሰጥቷችሁ ነበር። ምልክት ለመኑት። እስራኤል ምልክትን ለመነ። ለነቢዩ እንዲህ ብሎ ተናገረ። "የዘላለም ምልክት እሰጣቸዋለሁ፡ ድንግል ትፀንሳለችና። ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች።" (አሜን።) "**አማኑኤል** ይባላል፡ 'እግዚአብሔር ከኛ ጋር።'" እስካሁን የተሰጠ ታላቅ ምልክት ይህ ነው።

130 የሰማይና የምድር ፈጣሪ፡ የሆነው አምላክ፡ የፀሐይን ሥርዓት በሠራ ጊዜ። በፓሎማር ተራራ ላይ ቆማችሁ አማትራችሁ በማጉያ ስትመለከቱ፡ መቶ ሃያ ሚሊዮን የብርሃን አመታት ርቀት ማየት ትችላላችሁ። እስኪ ያንን ወደ ማይልስ ቀይሩት፡ ከዚያም አልፎ ጨረቃው፡ ከዋክብት፡ እና ዓለማትን ሁሉ፡ ፈጠረ። ልክ ከእጁ፡ **እንዲህ** አራግፎ የሰራቸው ናቸው። አዎን!

131 ይህ ታላቅ ፈጣሪም አዳኜ ሆኖልኛል። ወደ ትንሿ የደም ሕዋስ ወረደ፡ በወንድ ሳይሆን፡ በድንግልና ወደ ሴት መጣ፡ በሴቲቱም ውስጥ ከነበረው ትንሹ እንቁላል ወሰደ፡ እና መኖሪያ የሚሆነው ታናሽ ቤት ለራሱ አዘጋጀ። ኦህ፡ እ—እ—እስደናቂ ነው! ጀሆቫ! ጀሆቫ፡ የከብቶች እበት በተከመረበት ጉሮኖ ውስጥ፡ አለቀሰ። ያሕዌ፡ ገለባ ባለበት ግርግም። ይህ የዘላለም ምልክት ነው፡ ለአንዳንዶች ባለ-አእምሮ ሰዎች! ያሕዌ፡ እግዚአብሄር አምላክ፡ በሚሸት በረት ውስጥ የሚያለቅስ ጨቅላ (ሃሌሉያ!)። ከዚያም ስለራሳችን እንደሆነ ነገር ነኝ ብለን እናስባለን፡ አፍንጫችሁ ወደላይ ትቀስራላችሁ፡ ይዘንባል፡ ያስጥማችኋል፡ ከዚያም የሆነ ሰው ነኝ ብላችሁ እያሰባችሁ ትወጣላችሁ። ያሕዌ በበረት ውስጥ፡ እንደ ጨቅላ—እንደ ማንም ህጻን ልጅ፡ ፋንድያ ክምር ላይ... አለቀሰ። ሊያስደንቃችሁ ይገባል! ይህም ምልክት ነው። እግዚአብሔርም "የዘላለም ምልክት እሰጣችኋለሁ፡" ብሏልና። ያሕዌ፡ እንደ ብላቴና ተጫውቷል። ይህም ድንቅ ምልክት ነው። ያሕዌ! እንደ አናጢ እንጨት እየቆረጠ፡ በስራ ቦታ የሚሰራ፡ ያሕዌ። ሃሌሉያ! ማይ፡ ኦህ፡ ማይ! ያሕዌ፡ የዓሳ አጥማጆች እግር አጠበ። "ምልክትን እሰጣችኋለሁ።"

132 "ኦህ፡ ታውቃላችሁ፡ ካባዎች እና ማሰሪያዎች፡ አንገትጌዎች፡ እና ሌላ ያላቸው ቀሳውስት፡ መኖራቸው ግድ ነበር... " አያችሁ? ኦህ!

133 "የዘላለም ምልክት እሰጣችኋለሁ።" ያሕዌ፡ በግቢው አጥር ውስጥ ቆሞ ፊቱ ላይ ተተፍቶበታል። ያሕዌ፡ በሰው አካል፡ በሰማይና በምድር መካከል፡ ተንጠለጠለ። የመስቀልን ነውር ናቀ። ትንሽ ጨርቅ ጣል ያረግንበት ሐውልት አለ፡ ይህ ግን ቀራጺ የሰራው ነገር ነው። እርቃኑን ገፈፉት፡ አሳፈሩት! ኦህ፡ ያቺ ሰዓት በመጣች ጊዜ የግብዞች መንጋ! ይህች የሰው ቀን ናት፡ የጌታ ቀን ግን እየመጣች ትገኛለች። ያሕዌ! ያሕዌ፡ እየሞተ፡ አዎን፡ መልስ አልነበረም። ያሕዌ፡

እየጸለየ፡ መልስ አልነበረም። እህም። በትክክል። ሊያስደንቃችሁ ይገባል! የዘላለም ምልክት ነውና። ሰዎች ሁሉ ሊያውቁት የተገባ ምልክት ይህ ነውና። ከዚያም ሞተ፡ ያሕዌ ሞተ። ምድር መንቀጥቀጥ ጀመረች። ኦህ፡ ማይ!

134 ከዚያም ከመቃብር ተነሥቶ ወደ ላይ ዐረገ። ያሕዌ፡ በመንፈስ ቅዱስ መልክ በቤተክርስቲያኑ፡ በህዝቡ መካከል እንዲኖር ተመልሶ መጣ። ክብር! ጀሆቫ፡ የልብን አሳብ እያነበበ፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ ተመላለሰ። ጀሆቫ የታመሙትን ፈወሰ። ያሕዌ፡ ሰዎች እራሳቸውን መቆጣጠር እስኪሳናቸው ድረስ በሰው ከንፈር ተናገረ። ያሕዌ፡ እየተረጎመው እንደገና በኢንግሊዘኛ መጣ። ምልክት ትፈልጋላችሁን? አሜን! ያሕዌ ወደ ጋለሞታይቱ ወረደ፡ እሷንም አሰነሳት፡ ውሾች እንኳን ሊቀርቧት እስከማይችሉ-ድረስ እጅግ—የወረደችውን ሴት አሰነሳት፡ አጠባት እንደ በረዶም ነጭ አደረጋት እንደ ጽጌሬዳ የጠራ ልብ ሰጣት። ኦህ፡ ማይ! ያሕዌ፡ ጎዳና ላይ ወድቆ ዝንቦች አፉ ላይ የወረሩት ሰካራምን ከወደቀበት አስነሳ፡ ወንጌል ሰባኪ አደረገው... ?... የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ያነጻናል!

135 በምድር ላይ በነበረ ጊዜ፡ ወደ ዝቅተኛይቱ ከተማ ወርዶ፡ እጅግ ወደ ተዋረዱ ሰዎች ወረደ፡ እነርሱም እጅግ ዝቅተኛ ሰም ሰጡት። በትክክል። በጣም መጥፎ ነገር አድርገውበታል፡ "ብዔልዜቡል፡" ሰይጣን፡ በማለት በጣም መጥፎ ሰም ሰጡት። ሰው ሊሰጠው የቻለው፡ እጅግ ዝቅተኛ የሆነ ነገር ይህ ነው።

136 እግዚአብሔር ግን ከፍ ከፍ አደረገው፡ ሰማይን ለማየት ወደታች እስኪያይ ድረስ ከፍ ያለ ዙፋን ሰጠው። አሜን! ክብር! በሰማያትም በምድርም ውስጥ ከሚጠራው ሰም በላይ ከፍ ያለ ሰም ሰጠው፡ በሰማይ እና በምድር ያሉ ሁሉም በእሱ ሰም ይጠራሉ። ሰው ስለሱ ያሰበው ያ ነው፡ እግዚአብሔርም ስለሱ ያሰበው ያ ነው። አምላክ ሆይ፡ አሳቤ እንደ አሳብህ ይሁንልኝ፡ አባት ሆይ። አዎን፡ ወዳጄ። ውድ ሰም ሆይ!

137 አሁን፡ "በእኔ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው።" ስለዚህ፡ አንዲት አይነት የዘላለም ሕይወት ብቻ ካለ፡ እናንተም ካገኛችኋት በኢየሱስ ክርስቶስ በኩልም ከፈለግናት፡ የእግዚአብሔር ሕይወት ያቺ ናት። ከዚያም ያ የደም ሕዋስ በእግዚአብሔር ልጅ ላይ በተቆረሰ ጊዜ፡ ኢየሱስ ተብሎ በተጠራው በዚህ ሰው ውስጠኛው ክፍል የታሸገው ያ ትንሹ ያሕዌ (በእርሱ የመለኮት ሙላት በአካል የነበረ) እና አሁን **ያንን** ደሙን ለኃጢአታችን ሰርየት ሰንቀበለው፡ በእግዚአብሔር ላይ እንጂ፡ በሰው ላይ ያልነበረው ያንን መንፈስ... ክብር! መጽሐፍ ቅዱስ "የእግዚአብሔር ደም፡" በማለት ይጠራዋል።

138 አንድ ሰው ሲናገር "ይኸውልህ፡ አስተውል... አይሁዳዊ ስለነበር፡ ስለ አይሁዶች አትናገር፡" አለኝ። አይሁዳዊ አልነበረም። አምላክ እንጂ፡ አይሁዳዊም አህዛብም አልነበረም። በትክክል። የተፈጠረ ደም ነበር። እግዚአብሔር ልዩ አድርጎታል። የገዛ ገንዘቡ ነበርንና፡ ሞትን ስለእኛ ስለሞተ በተፈጠረው ደም በኩል ይቅርታን ተቀበልን። ያንን የደም ሕዋስ በተቆረሰ ጊዜ፡ ወደ እኛ ተመልሶ ይመጣ ዘንድ መንፈስ ቅዱስን ፈትቶ ለቀቅልን፡ እና አሁንም በመንፈስ በመወለድ የእግዚአብሔር ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ሆነናል። ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔር የራሱ የነበረው፡ ማለት መጀመሪያም ሆነ ፍጻሜ አልባ

የሆነው ህይወቱ፡ በእግዚአብሔር ጸጋ በኢየሱስ ክርስቶስ የእኔና የእናንተ ነው። ይኸው ነው።

139 አሁን፡ “ሲኦል፡” ከአፍታ በኋላ እንመለሰበታለን። እላችኋለሁ—በምንም ቢሆን... በሚቃጠል ሲኦል እምናለሁ። አዎን፡ እምናለሁ፡ መፅሃፍ ቅዱስ፡ የእሳት ባህር ይለዋልና። አሁን፡ በምንም ቢሆን ግን ይህ ዘለአለ-... ዘላለማዊ ሊሆን አይችልም። ምናልባት... መጽሐፍ ቅዱስ ዘላለማዊ ነው በጭራሽ አላለም፡ “ለዘመናት” ሲኦል ይለዋል። ኢተርናል የሚለውን ቃል አይልም፡ “ለዘመናት” ሲኦል እንጂ። ይህም፡ ለዲያብሎስ እና ለመላእክቱ የዘጋጀላቸው ነው፡ ለብዙ ዘመናት የሚቆይ ሲኦል እንጂ፡ ዘላለማዊ አይደለም። እንግዲህ፡ አሁን... ያቺ ነፍስ ስለስራቸው ስራ ምንላብታ አስር ሚልዮን ዓመታት ልትሰቃይ ትችል ይሆናል፡ የማውቀው ይህ ነው። በእግዚአብሔር ዕይታ ለብዙ **ዘመናት** ምን ሊሆን እንደሚችል አላውቅም። ለአምስት ደቂቃ ሊሆን ይችላል፡ ለአንድ ሚሊዮን ዓመታት ሊሆን ይችላል፡ ለአሥር ሚሊዮን ዓመታት ሊሆን ይችላል፡ ነገር ግን ያቺ ነፍስ የምትጠፋበት ጊዜ ይመጣል።

140 መጽሐፍ ቅዱስ የተናገረው ይኸውና፡ እያችሁ፡

### ... ድል የነሣው በሁለተኛው ሞት አይጎዳም።

141 የመጀመሪያው ሞት ከምንወዳቸው ሰዎች መለየት ነው። ወደ እግዚአብሔር መገኘት እንሄዳለን፡ ከመገኘቱ ፈጽሞ አንወጣም። እያችሁ? እንግዲህ፡ ሁለተኛው ሞት ካለ፡ ያ የነፍስ ሞት መሆን አለበት። በተጨማሪ ዓለምን ያሸነፈ፡ ወይም የዓለምን ነገሮችን ያሸነፈ፡ የዘላለም ሕይወት አለው እና ሁለተኛው ሞት አይነካውም። ይኸው የዘላለም ህይወት፡ ይህ ነውና። ኃጢአተኛው—ግን... መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡ “በተድላ የምትኖር ሴት በህይወት እያለች የሚተች ናት።” ልክ ነው? “ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ በእርግጥ ትሞታለች።” **መሞት** ምንድን ነው? ሙሉ በሙሉ “መለያየት፡” “በቃ አለቀ።” እያችሁ? ከእንግዲህ፡ ተቆርጧል፡ ይህ ነው። ተቆርጧል፡ ሌላ ዕድል የለውም። ያንን ምን ያህል ጊዜ ይዘልቃል? እሱ በገባበት በተመሳሳይ መንገድ ይወጣል፡ ምንም ነገር እስከማይቀርለት ድረስ ወደ አንድ ነገር ይደርሳል። እሱ አስቀድሞ ወደተሰራበት ሁኔታ ይመለሣል።

142 ወደ መጀመሪያው ሕዋስ እስክትወርድ ድረስ፡ ሕዋሱን ወሰደን፡ ሕዋሱን ወደ አንድ ሕዋስ፡ ወደ ሌላ ሕዋስ ልንቆርሰው እንችላለን፡ ወደዚያ ሕዋስ ውስጥ ቆርሰነው፡ ከዚያም የደም ኬሚስትሪ እናገኛለን፡ ወደ ደሙ ልዩ ኬሚስትሪ ትገባላችሁ፡ ከዚያም በዚያ ሕዋስ ውስጥ ወደሚገኘው ታናሽ ክፍል ትደርሳላችሁ፡ ህይወት ያ ነው። ስለዚህኛው ምንም አያውቁም። በምንም አያገኙትም። ስለዚህ፡ ያቺ ህይወትም በስተመጨረሻ በቃ ወደማትገኝበት ሁኔታ ትደርሳለች፡ የዚያ ህይወት ኬሚስትሪ፡ ምንም አይነት ኬሚስትሪ አለው ብዬ አላምንም። መንፈሳዊ ይሆናል እንጂ።

143 ከዚያ በኋላ፡ በዚያ ሂደት ውስጥ፡ ሙሉ ለሙሉ ይለያያል በመጨረሻም አይገኝም። መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውም ይህ ነውና፡ “ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ፡ እርስዋ ትሞታለች።” “እናም በእነዚህ በቤተ ክርስትያን ዘመናት ድል የሚነሡ ሰዎች **በሁለተኛው** ሞት አይጎዱም።” ሥጋው ቀድሞ ይሞታል፡

ነፍስ ቀጥላ ትሞታለች ከዚያም በኋላ አይገኛም። አያችሁ? ያ ነው… ይህን የሚናገረው መጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ ታምናላችሁ?

144 አሁን አስታውሱ፡ ሲኦል ዘላለማዊ ከሆነ፡ መጽሐፍ ቅዱስ "ሲኦል የተፈጠረ ነው፡" ማለቱ ስሕተት ነው። እናም አንድ ሰው በሲኦል ውስጥ ለዘላለም የሚቃጠል ከሆነ፡ እንግዲያውስ ለመቃጠልም፡ ንቃተ ሕሊና ያለው ዘላለማዊ መሆን ይኖርበታል። ልክ ነው? እሺ፡ ስንት አይነት ዘለአለማዊ ህይወት አለ? አንድ ብቻ። በትክክል። አንድ ዘለአለማዊ ህይወት ብቻ።

145 አሁን፡ አልፋችሁ ሄዳችሁ "ወንድም ብራንሃም በሲኦል መኖር አያምንም፡" እንዳትሉ አደራ። ወንድም ብራንሃም በሲኦል ያምናል። መጽሐፍ ቅዱስ ሲኦል እንዳለ ያስተምራል። ልክ የእረፍት ቦታ—እንዳለ ሁሉ፡ የቅጣት ቦታ—መኖሩ ግድ ነው። እግዚአብሔርም በእርሱ ላይ ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ እንድትቀጣ ያደርጋታል። ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኛችሁ ባለመቀበላችሁ ምክንያትም፡ በእርግጥ ትቀጣላችሁ። ከዚያ በኋላ ግን የማትኖሩበት ጊዜ ይመጣል። ወደዚያ ሁኔታ ለመመለስ ስንት ሚሊዮን ዓመታት እንደሚፈጅብህ ግን፡ እኔ አላውቅም። ጊዜ ግን አለ…

146 ዳግመኛ እስክትወለድ ድረስ የጊዜ ሰብዕና ነህ፡ ከዚያ በኋላ ግን ዘላለማዊ ሰብዕና ነህ። እና የዘላለም ህይወት ማግኘት የምትችሉበት ብቸኛው መንገድ የእግዚአብሔር የአካሉ ክፍል በእናንተ ውስጥ ሲኖር ነው። ይታያችኋል? በትክክል።

**መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን፡ ጆሮ** ያለው **ይስማ፡…**

147 እወደዋለሁ። እናንተም አይደል? የዘላለም ሕይወት በማግኘቴ በጣም ደስተኛ ነኝ። አሁን የዘለአለም ህይወት ስላለን፡ ያ ከአሁን በኋላ አያስቸግረኛም። እንዲሁም ደግሞ ይህን አውቃለሁ፡ ሁላችንም፡ እንደምናገኛት አልጠራጠርም።

148 ስለ፡ ኢራኔዎስ፡ "ይህን ታሪኩን ለማንበብ፡" አዎን፡ ስለ ኢራኔዎስ የጻፍኩት ማስታወሻ ይዣለሁ። ኢራኔዎስ የተመረጠበት ምክንያት የጴንጤቆስጤ (የመጀመሪያው) ቤተክርስቲያን ምልክቶች ከእሱ ጋር ስለነበሩ ነው።

149 አሁንም፡ እግዚአብሔር… የቤተክርስቲያን መጀምሪያ በጴንጤቆስጤ ቀን መሆኑ የምታምኑ ስንቶች ናችሁ? በጣም ጥሩ። እግዚአብሔር በጴንጤቆስጤ ቀን ቤተክርስቲያንን እንደባረካት የምታምኑ ስንቶች ናችሁ? በጣም ጥሩ፡ ወዳጄ። የእግዚአብሔር የመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን ያቺ ከሆነች እንግዲያውስ "ቤተ ክርስቲያን" የሚላት እሷን ነዋ፡ እንግዲኢህ እሱ የወይኑ ግንድ ነው፡ እኛም ቅርንጫፎች ነን፡ ወይኑ ሌላ ቅርንጫፍ ቢያወጣ ግን፡ ምን ይሆናል? ጴንጤቆስጤ። አዎን! ምናልባት አሁን፡ በስም ላይሆን ይችላል። አሁንም ጴንጤቆስጤ **መጠሪያዎች** አሉ፡ ነገር ግን ከሜቶዲስት፡ ባፕቲስት፡ ፕሪስባይቴሪያን፡ ጴንጤቆስጤ ከሚባሉት የዘለለ አይደለም። ያ ማለት ምንም ማለት አይደለም፡ አያችሁ፡ ያ ስም ብቻ ነው። ነገር ግን የዘላለም ሕይወትን የሚሰጣችሁ፡ የጴንጤቆስጤ ልምምድ በልባችሁ፡ ጴንጤቆስጤ በነፍሳችሁ እስካላችሁ ድረስ፡ "በሁለተኛው ሞት ፈጽማችሁ አትጎዱም፡" በማለት እግዚአብሔር ቃል ገብቶላችኋል፡ ይህም፡ የዘለአለም ህይወት

ስላላችሁ በሁለተኛው ሞት **አትጎዱም** ነው። አያችሁ? እንዲህ ናችሁ... ይህ ይኖራችኋል...

150 "ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ።" አሁን፡ አሳታዝኑት (የተሳሳቱ ነገሮችን አታድርጉ)። ካሳዘናችሁት፡ ዋጋ ትከፋላላችሁ፡ መጽሐፍ ቅዱስም ይናገራልና፡ "እስከ ቤዛችሁ ቀን ድረስ የታተማችሁበትን የእግዚአብሔርን ቅዱስ መንፈስ አታሳዝኑ።" ልክ ነው? "መንፈስ ቅዱሰን አታሳዝኑ።"

151 አቤት! ከዕለታት አንድ ቀን፡ እንዲ ማለዳ፡ ድንቅ ቀን ይሆናል። ትንሣኤ ዓለም አቀፋዊ እንደሚሆን ያሳይ ዘንድ፡ "ሁለቱ በእርሻ ይሆናሉ፡ አንዱንም እወስዳለሁ፡ ሁለት አልጋ ላይ ይተኛሉ፡ አንዱን እወስዳለሁ።" እነሆ፡ በአንደኛው ሰፍራ ሌሊት፡ በምድር ሌላኛው ክፍል ብርሃን ይሆናል፡ ዓለም አቀፋዊ ትንሣኤ፡ ንጥቀት ይሆናል። የእግዚአብሔር መለከት ይነፋል፡ እናም **እዚህ፡ እዚህ፡ እዚህ** ያሉትን እነዚህ፡ የዚህች ትንሽ ቤተክርስቲያን የሆኑት ሁሉ፡ እንዲሁም **በዚያ** ሁሉ አልፋ፡ **እዚህ፡ እዚህ፡ እዚህ** የመጣችው መንጋም ጭምር።

152 ያቺ ድንግል፡ ያቺ ድንግል በሰባተኛው ክፍለ ጊዜ ያንን ባየች ጊዜ... አሁን፡ አስታውሱ ሰባት ደናግል ነበሩ። ልክ ነው? ወይም፡ አምስት ደናግል ወጡ፡ ማለቴ ነው... ጌታን ሊቀበሉ አሰር ደናግል ወጡ፡ አምስቱ ልባሞች አምስቱም ሰነፎች ነበሩ። ልክ ነው? አሁንም፡ ስለ ክፍለ ጊዜዎቹ፡ ሰባት ክፍለ ጊዜዎች ነበሩ። እና በሰባተኛው ሰዓት መጨረሻ (አንዳንዶች በ**ዚህኛው** ክፍለ ጊዜ ተኙ፡ **ይህኛው**፡ **ይህኛው**፡ **ይህኛው**፡ እና **ያኛው**፡... )፡ በሰባተኛውም ክፍለ ጊዜ፡ ድምፅ መጣ፡ "እነሆ፡ ሙሽራው መጣ፡ ልትቀበሉት ውጡ።" ተነሥተው መብራታቸውን አዘጋጁ። እና እነዚህ ሁሉ **ወደዚያ** ተነሱ። እነሆ፡ ድንቅ ጊዜ አይሆንም ወይ!

እነሆ፡ የምንዘምራት መዝሙር ነበረች፡

ድንቅ ጊዜ ነው ለአንተ፡
እንዴት ድንቅ ጊዜ ነው ለእኔ፡
ንጉሳችን ኢየሱስሰን ለመገናኘት ከተዘጋጀን፡
እንዴት ያለ ድንቅ ጊዜ ይሆንልናል።

እዚህ፡ ይህን መዘመር ከቻልን እስኪ እንየው፡

ድንቅ ጊዜ ነው ለአንተ፡
ድንቅ ጊዜ ነው ለእኔ፡
ንጉሳችን ኢየሱስሰን ለመገናኘት ከተዘጋጀን፡
እንዴት ያለ ድንቅ ጊዜ ይሆንልናል። (የሚደንቅ አይሆንምን ወይ? )

እነሆ፡ ድንቅ አይሆንም ወይ፡
የሚሸከሙት ሸክም የሌለበት?
ከልብ-ቃጭሎች ጋር በደስታ ስንዘምር፡
እነሆ፡ ድንቅ አይሆንም ወይ?

153 ስንቶቻችሁ ወደ ቤት እንደምትገቡ ታውቃላችሁ? በዚያ በር እንደምትወጡ ስንቶች ታውቃላችሁ? አታውቁም። ወጥታችሁ በድጋሚ እንደምትመለሱ

ስንቶች እርግጠኞች ናችሁ? መገመት አትችሉም። ስለዚህ ይህ ሌሊት እንዲያልፋችሁ አትፍቀዱ፡ በዚች ሌሊት እግዚአብሔርን አይለፋችሁ፡ ምናልባት ይህ ምሽት ጊዜ ወይም እድል የምታገኙበት የመጨረሻ ምሽት ሊሆን ይችላል። ኧረ እንደው፡ እነማን ትባላላችሁ? ከወዴትስ መጣችሁ? ወዴትስ እየሄዳችሁ ነው? በዓለም ውስጥ ይህ ምን እንደሆነ ሊነግራችሁ የሚቻለው ብቸኛው መጽሐፍ፡ የተባረከው ጥንታዊ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው። እኛም የምናምነው መፅሃፍ ቅዱስ ያ ነው፡ የምናምነው አምላክ ያ ነው።

154 እና ወደዚያ ሙሽራ ካልገባችሁ፡ ወደዚህች ታናሽ መንጋ ካልደረሳችሁ፡ **ወደዚህች** በተቋማት እና በሐይማኖት መግለጫዎች ወደምትጨናነቀው፡ ወዘተረፈ፡ በዚህች ታናሽ መንጋ ውስጥ ካ—ካ—ካልገባችሁ… እንግዲህ፡ ይህን ተበርናክል መቀላቀል፡ ወይም ምንም አይነት ነገር ውስጥ መግባት አይጠበቅባችሁም፡ ማድረግ ያለባችሁ ወደ መንግስቲቱ መወለድ ነው። አሁንም፡ በሜቶዲስት፡ ባፕቲስት፡ ፕሪስባይቴሪያን፡ ወይም በፈለጋችሁት ሰፍራ ህብረት ማድረግ ከፈለጋችሁ፡ ያ የእናንተ ውሳኔ ነው። ኣያችሁ፡ ከወደዳችሁት ጋር ሕብረት ማድረግ ትችላላችሁ። አንድ ነገር ግን እነግራችኋለሁ፡ ዳግም ስትወለዱ፡ እንደምታውቁት፡ "ተመሳሳይ ላባ ያላቸው ወፎች… " ማይ!

155 አንድ ሰው አንድ ጊዜ ጠየቀኝ፦ "ወንድም ብራንሃም፡ ሰዎቹን፡ 'ወደ ሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን ተመለሱ አልካቸው፡'" አለኝ።

እኔም፡ "አዎን። ያባርሯቸውና፡ መሄጃ አይኖራቸውም" አልኩት። ከዚያ በኋላ እናያቸዋለን…

ምንም ችግር የለም፡ ሂዱ ተመለሱ፡ ብዙም ሳይቆይ፡ ታዩታላችሁ። ብዙም ሳይቆይ፡ ወዲያው ይመለሳሉ።

156 ታውቃላችሁ፡ አንድ ጊዜ በ… ኖህ… በነበረበት በደህንነት ስፍራ፡ መርከብ ውስጥ፡ በኖህ፡ ያኔ ታላቅ ጎርፍ መጥቶ ነበር። ኖኅም ቁራውን ከመርከቧ ውስጥ አወጣውና፡ ዝም ብሎ እየጮኸ እየዞረ በዚያው ሄደ። ለምን፡ በዚያው ረክቶ ነበር፡ ከመጀመሪያም ጥንብ አንሣ ስለነበረ ነው። ከአንድ የጠነባ ሬሳ በርሮ፡ ሆዱ እስኪቀደድ ድረስ ከዚህኛው ከበቅሎ ተመግቦ፡ እናም ወደዚያ ሄዶ— ከዚያ ከጠነባው በግ ሆዱ እስኪቀደ ድረስ ይበላል፡ እንዲሁም ከዚያም ያልፋል፡ ሁሉም ዓይነት የጠነቡ ሬሳዎች ወዳሉበት ዙሪያ ይጓዛል።

157 ስለዚህ ቁራው አንዱ ዙርያ ላይ ቁጭ ብሎ እንዲህ እየዘፈነ፡ "ኧረ በለው፡ የራሴ ኢዮቤልዩ እያደረግኩኝ ነው!" መዝፈን ይችላል።

158 ትንሿን እርግብ ወደ ውጭ በላኳት ጊዜ ግን፡ የተለየ ተፈጥሮ ነበራት። ከባድ ጠረን ስለሆነ፡ እሷ "ልትቋቋመው አልቻለችም። እህም!" ለምን? ርግብ ሐሞት የላትም፡ ሀሞት የሌለበት ወፍ እሷ ብቻ ናት። ምግቡን መፍጨት ስለማትችል፡ ማድረግ የምትችለው ብቸኛው ነገር ወደ መርከቡ ተመልሳ በሩን ማንኳኳት ብቻ ነው።

159 እናንተም ወደ ፈለጋችሁት ቦታ ሂዱ። የምጠይቃችሁ ነገር ቢኖር ወደ መንግስቱ ተመልሳችሁ እንድትመጡ ነው፡ ወዴት እንደምትሄዱ አውቃለሁና። ከእንግዲህ ያን መቋቋም አይቻላችሁም፡ ወንድሜ ሆይ፡ ያኔ እንዲህ ትላለህ፦ "የመለያያውን መስመር አልፌዋለሁ፡ ይህን አለም ወደ ኋላ ትቻለሁ።" አዎን፡ ወዳጄ። እርግጥ ነው።

እነሆ፡ በላይኛው ሰገነት ተሰብስበው፡
በስሙ ሲጸልዩ ተግተው፡
በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀው፡
ወጡ የአገልግሎት ኃይል ተቀብለው፡
ለእነርሱ ያደረገላቸው በዚያ ቀን
አሁንም ያደርግላችኋል ያው ነው፡
አንዱ ነኝ ማለቴ ደስተኛ ነኝ። (እናንተስ? )

አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ ነኝ... ማለቴ ደስተኛ ነኝ፡ (ሃሌ ሉያ!)
አንዱ ነኝ፡ እኔም አንዱ ነኝ፡
አንዱ ነኝ ማለቴ ደስተኛ ነኝ።

በዛሬ ቀን ሰንቶች ደስ ብሏችኋል? ኦህ፡ ማይ!

ና፡ ወንድሜ፡ ፈልገው ይህን በረከት
ልብህን የሚያነጻ ከሐጢያት
ቃጭሎቹን-ሁሉ ያስዘምራል
የነፍስህን ነበልባል ሁሌ ይጠብቃል፡
እነሆ፡ በልቤ ውስጥ ይነዳል አሁንም፡
እነሆ፡ ክብር ይሁን ለእርሱ ስም፡
አንዱ ነኝ... ማለቴ ደስተኛ ነኝ።

አንዱ ነኝ፡ እኔም አንዱ ነኝ፡
አንዱ ነኝ... ማለቴ ደስተኛ ነኝ፡ (ሃሌ ሉያ!)
አንዱ ነኝ፡ አንዱ ነኝ፡
አንዱ ነኝ ማለቴ ደስተኛ ነኝ።

160 አሁን ይህን የሚቀጥለውን አዝማች በምንዘምርበት ጊዜ፡ ዘወትር ምሽት እንደምታደርጉት፡ እጆቻችሁን እንድትጨብጡ እፈልጋለሁ፡ ሜቶዲስቶች፡ እና ባፕቲስቶች፡ እና ፕሪስባይቴሪያኖች ሁላችሁም። እርስ በርሳችሁ ተጨባበጡ፡ እንደው ከቻላችሁም፡ አንዳችሁ የሌላውን ማስቲካ ማኘክ እስክትችሉ ድረስ ወዳጆች ሁኑ። አሁን ይህን ስንዘምር፡ የእውነት፡ እውነተኛ ወዳጅ ተግባቢዎች ሁኑ፡

አንዱ ነኝ፡ እኔም አንዱ ነኝ፡
አንዱ ነኝ ማለቴ ደስተኛ ነኝ፡
አንዱ ነኝ፡ እኔም አንዱ ነኝ፡
አንዱ ነኝ ማለቴ ደስተኛ ነኝ።

ያልተማሩ ቢሆኑ በዚህች ዓለም፡
የሚያውቃቸው ማንም ባይኖር፡
መንፈስ ቅዱስ ተሞልተዋል
ተጠምቀው በኢየሱስ ስም፡
ለቀረበም፡ ለራቀውም ይነግራሉ
ኃይሉ አሁንም ያው ነው ብለው፡
አንዱ ነኝ ማለቴ ደስተኛ ነኝ...

እስኪ አሁን በደንብ እንዘምረው፡

ኦህ፡ አንዱ ነኝ፡ እኔም አንዱ ነኝ፡
አንዱ ነኝ… ማለቴ ደስተኛ ነኝ፡ (ሃሌ ሉያ!)
አንዱ ነኝ፡ እኔም አንዱ ነኝ፡
አንዱ ነኝ ማለቴ ደስተኛ ነኝ።

161 ከሰምርኔስ ጋር ለእርሱ ሰማዕት ለመሆን ፈቃደኛ ትሆናላችሁን? ሞትን እንድትቀበሉ ወይም እንዳትቀበሉ የሚያስገድዳችሁ ሰፍራ ከደረሳችሁ፡ ፊት ለፊት ትጋፈጣላችሁን? አዎን፡ ወዳጄ። አምላክ ሆይ፡ ደስታዬ ነው። አዎን፡ ወዳጄ። እኔ መሞት የምፈልገው እዚሁ፡ ፑልቢቱ ላይ ነው። ይህ እውነት ነው። እንደው የተረዳሁት ይመስለኛል እና በቅርብ ጊዜ የሆነ ነገር ነው ጀርመን አገር ውስጥ ሊያገኙት ነበር። ኦህ፡ በሌሊት መነጽር ሊተኩሱብኝ ነበር፡ እና የጀርመን ወታደሮች በፍጥነት ዙርያዬን ከበው **እንዲህ** መለሱት። “እዚሁ መሰክ ላይ ለጌታዬ መሞት ምንኛ ድንቅ ነገር ነው!” ብዬ አሰብኩ፡ ኦህ፡ ማይ! እንዴት—እንዴት ያለ ድንቅ ነገር ነው!

162 እሺ፡ አጭር መዝሙር ልዘምርላችሁ። ልዘምር? አጠር ያለች ዝማሬ ለመዘመር—ጊዜ ይኖራችኋል? በጣም ጥሩ። እኔ'እንኳ እናገረዋለሁ እንጂ፡ አልዘምረውም። አቤት፡ መዘመር ሁሌ ምኞቴ ነበር። ከእነዚህ ቀናት ውስጥ አንድ ቀን በገነት ወዳለው ግዙፍ እና ተወዳጅ ቤታችሁ ስትደርሱ፡ ታውቃላችሁ፡ በጫካዎቹ ወደ ታች መጨረሻው ላይ፡ እኔ እና ሩሰል ክሪች አደን በምናድንበት። በጫካው መጨረሻ ላይ ወንድም ኔቪል እንዲህ እያለ የሚዘምርላት ትንሽ ጎጆ አለች፡ **በክብር አገር፡** (ስለ ቦታዬ የሚናገር መስሎኝ ነበር።) **አንዱ ጥግ ላይ ጎጆ ሰራልኝ።** ከዕለታት አንድ ቀን በተላላቆች በረንዳዎች በአንዱ ላይ ስትንጎራደዱ፡ ዙርያውንም እንዲህ ስትቃኙ፡ ምናልባት ወዲያ ማዶ እንዲህ እያለ የሚዘምር ሰው በሰማችሁ ጊዜ፡

አስገራሚው ጸጋው! እንዴት ግሩም ነው፡
እንደኔ ዓይነት ጎሰቋላ ያዳነው!

163 እንዲህ ትላላችሁ፡ “ጥሩ ነው፡ እግዚአብሔርን ይባርክ፡ ወንድም ብራንሃም በደንብ ቻለ። ይኸው በዚያ ማዶ ቆሞ፡ **አስገራሚው ጸጋ**፡ ሲዘምር ሰማሁት።”

164 ወደዚያ የሚያመጣኝ አስገራሚው ጸጋ ይሆናል። ትክክል ነው።

ግን ያንጠባጠባል ደሙ፡ አዎን፡ (ለዚህ ነው ይህንን የምሰብከው።) ያንጠባጠባል ደሙ፡
ይህ የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል ያንጠባጠባል ደሙ፡
ስለ እውነት የሞቱ የደቀ መዛሙርት ደም፡
ይህ የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል አሁንም ያንጠባጠባል ደሙን።

ለዚህ የመንፈስ ቅዱስ እቅድ መጀመሪያው የሞተው፡
መጥምቁ ዮሐንስ ነበር፡ እርሱ ግን እንደ ወንድ ሞተ፡
ከዚያም ጌታ ኢየሱስ መጣ እርሱንም ሰቀሉት፡
መንፈስ ሰዎችን ከኃጢአት እንደሚያድናቸው አስተምሯል።

ጴጥሮስና ጳውሎስ፡ ዮሐንስ ዘመለኮትም ነበሩ፡
ይህ ወንጌል እንዲያበራ ሕይወታቸውን የሰጡ፡
እንደ ጥንት ነቢያት፡ ደማቸውን ቀላቀሉ፡
እውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል በንጽሕና ይነገር ዘንድ።

ከመሠዊያው በታች ያሉ ነፍሳት (እነዚህ ሰማዕታት) “እስከ መቼ? ” ይላሉ፡
ጌታ የበደሉትን ይቀጣ ዘንድ አለውና፡ (ቶሎ! ሰሙት!)
ይሁን እንጂ የሕይወታቸውን ደም የሚሰጡ ገና ብዙ አሉ
ለመንፈስ ቅዱስ ወንጌል እና ለሚፈሰው አለላ።

ያንጠባጥባል ደሙ፡ አዎን፡ ደሙን ያንጠባጥባል፡
ይህ የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል ያንጠባጠባል ደሙ፡ ይህ የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል ያንጠባጠባል ደሙ፡
ስለ እውነት የሞቱ የደቀ መዛሙርት ደም፡
ይህ የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል አሁንም ያንጠባጠባል ደሙን።

165 ኦህ፡ የሚሆን ነገር አለ...

[አንዲት እህት በልሳን ተናገረች፡ ሌላ ወንድምም ተረጎመው። ሌላ ወንድምም በልሳን ተናገረ፡ ሌላ እህትም በልሳን ተናገረች። በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ። አንድ ወንድም ተረጎመው—አርታዒ።] ክብር። አሜን። አሜን። እህም። እህም። ክብር። አሜን። አዎን።

166 ኣሜን። “መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይሰማ።”

እወደዋለሁ...

አሁን አምልኩት፡ ምን እንደሚያደርግ ተመልከቱ። ከዚህ በፊት እሱን የማትወዱት ከነበራችሁ፡ አሁን እሱን መውደድ ትፈልጋላችሁን? እንደ አዳኛችሁ ለመቀበል፡ ተነሥታችሁ እውቅናን ትሰጡታላችሁን?

... እንደወደደኝ፡ (እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወንድሜ።)
የገዛው...

እንዲህ ቆሞ፡ “እፈልገዋለሁ፡ አሁን፡ እሱን መውደድ እፈልጋለሁ፡” የሚል ሰው አለን?

... መዳኔ
በቀራንዮ...

እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እህቴ። እዚያ ጋ እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ ወጣቷ ሴት።

እወደዋለሁ...

መንፈስ ለቤተ ክርስቲያን የሚለው፡ ጆሮ ያለው ይሰማ።

... መጀመሪያ ወደደኝ
መዳኔንም ገዛሁ
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

167 የሰማይ አባታችን ሆይ፡ እነዚህ ሦስቱ በእግራቸው ቆመው ሰታያቸው፡ አምላኬ ሆይ፡ አንተ ዘለአለማዊ ሆይ፡ ምሕረትን እንድታደርግ እለምንሃለሁ፡ እና የኃጢአትን ሁሉ ሰርየት፡ መዳን፡ እና መንፈስ ቅዱስን በሕይወታቸው ሰጣቸው፡ ይህም በሁለተኛው ሞት እንዳይነኩ ነው። ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታ፡ እዚያ እንደቆሙ፡ በደጅ እንደቀረበ፡ አንዳች ነገር—ተገንዝበውታልና። መንፈስ ቅዱስ ማስጠንቀቂያ ሰጥቷልና። የእግዚአብሔር መንፈስ በሰዎች መካከል ሲወርድ መመልከት፡ ልክ እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት ሲሰራ መመልከት፡ ሶስቱን መልእክቶች ብቻ እና ይደመድሙታል። አምላክ ሆይ፡ ለእያንዳንዱ ሰው መልእክት ነው።

168 አሁንም፡ አባት ሆይ፡ ሰለ ምሕረትህ እንጸልያለን። ውድ መንፈስህ በመካከላችን ይኑር። እናክብረው ዘንድ፡ አምላክ ሆይ፡ ሰጠን። እነዚህ ነፍሳት ተቀበላቸው፡ አባት ሆይ፡ የዛሬው ምሽት መልዕክት ፍሬዎች ናቸው፡ ይህም በመካከላችንም የተነገረው የመንፈስ ቅዱስ መልእክት ነው። እግዚአብሄር አባት ሆይ፡ በህይወት ዘመናቸው ሁሉ ከእነርሱ ጋር እንድትሆን፡ እንጠይቃለን። በዚያም “ፍጻሜ በሌለባት ዓለም” በክርስቶስ ደም እና በጸጋው ድነው፡ መገናኘት ይሁንልን። አሁንም አባት ሆይ፡ ወደ አንተ እናቀርባቸዋለን፡ በመንፈስ ቅዱስህ ሙላቸው። በኢየሱስ ስም ጸለይን። ኣሜን።

169 እግዚአብሔር ይባርካችሁ፡ ወንድሞቼ። በቆማችሁ ክርስትያኖች፡ አጠገባችሁ የቆመውን ሰው ሁሉ፡ ቁጭ ሲሉ እጆቻቸውን ጨብጡ፡ ባርኳቸው… መልካም የእግዚአብሔርን ጅማሬ በሏቸው።

170 መንፈስ ቅዱስ ምን ያህል ታዛዥ እንደሆነ፡ በስተመጨረሻ እንዴት እንደሚያደርገው አይታችኋል? አይታችኋል? መጽሐፍ ሲናገር፡ “በልሳን የሚናገሩ… ሁለት ሆነው ይናገሩ፡ ወይም አይደለም… ቢበዛ ሶስት ይሁኑ፡” አያችሁ። መልዕክቱ የመጣው ስብከት መሃል እያለሁ አይደለም፡ ሁሉ ካለቀ በኋላ ነው። መሆን ያለበትም በዚያ መንገድ ነው፡ ሰው ሁሉ በትህትና መንፈስ የሚናገረውን አዳምጧል። ከዚያስ ምን ተፈጠረ? ኃጢአተኞች ንስሐ ለመግባት ተነሱ። ኧረ፡ አስቡ እስኪ። ባይገባቸውም… መንፈስ ቅዱስ በራሱ፡ በቃሉም በኩል፡ መጥቶ ተገለጠ።

171 በልሳን ከሚናገሩት ሰዎች አንዳንዶቹን አውቃችኋለሁ፡ የተናገሩትን ሦስቱንም አውቃችኋለሁ፡ እና—ትርጓሜ የሰጡትን አውቃችኋለሁ፡ ሕይወታቸው በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት የለሽ እንደሆነ አውቃለሁ። ፓስተራችን፡ ወንድም ኔቪል፡ የሜቶዲስት አገልጋይ፡ የሜቶዲስት አገልጋይ ነው፡ እዚህ ቦታ ላይ፡ መንፈስ ቅዱስን ተቀበለ። ጁኒዬ፡ እዚህ ጋር ያለው፡ ወንድም ጃክሰን፡ ሌላው የሜቶዲስት ሰባኪ፡ መንፈስ ቅዱስን ተቀበለ። ልክ ነው፡ በልሳኖች እና በትርጓሜዎች ሰጦታ ተቀብሏል።

172 እና እግዚአብሔር ሲናገር፡ በቤተክርስትያን ያለው ሁሉ፡ እንዴት በትህትና እንደነበረ አስተውላችኋል። ልክ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል እንዴት እንደሚናገር አይታችኋል፡ አንድ፡ መልዕክቱ በአንድ አላቆመም፡ በድጋሚ ተናግሯል፡ ይሁን እንጂ ከሶስት ጊዜ በላይ አይናገረውም፡ አይታችኋል፡ ልክ እንደ ቅዱሳን ቃላት ነው። አያችሁ፡ መልዕክቱን ይሰጣል፡ በጭራሽ አያስረውም፡ “የነቢያት መንፈስ ለነቢያት ይገዛልና።” ሌላው ሁሉ በጸጥታ ያዳምጣል…

173 አሁንም ቤተ ክርስቲያን በሥርዓት መሆን ያለባት በዚህ መንገድ ነው። አሁንም ለእናንተ ከውጪ ልትሆኑ ለምትችሉ ሰዎች፡ ሰናገር ሰምታችኋል፡ እንደዛ መሆን አለበት። እያችሁ፡ መልዕክቱ አለቀ። ከዚያም ፍሬውን እዩት? **ወዲያውኑ** ተፈጸመ። ልክ እንደ መለየት ወይም ሌላ መንፈስ፡ የሆነ ነገር ተከናወነ። ድንቅ አይደለምን? ኦህ፡ በቅዱስ ጳውሎስ የተደነገገውን ተመሳሳይ ነገር **እዚህ** በማየቴ፡ በጣም ደስ ብሎኛል፡ **እዚህም** ድረስ አልጠፋም። አሁንም ተመሳሳይ ነገር ነው። ኦህ፡ እኔም አንዱ ነኝ በማለቴ ደስተኛ ነኝ። እናንተስ? በጣም ጥሩ።

174 እንግዲህ፡ ነገ ማታ ሰባት ሰዓት ላይ፡ የሎዶቅያን ዘመን እንማራለን፡ ያም **የጋብቻ** ዘመን ነው። ከቻላችሁ እንድትመጡ እጋብዛችኋለሁ። ዛሬ ማታ ትንሽ አርፍጃለሁ፡ ምናልባት መንፈስ ቅዱስ ስለመናገሩ ወዘተ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ አሁንም ገና ነው፡ ዘጠኝ ሰዓት ከሃያ ብቻ ነው። እናም ብዙውን ጊዜ እዚህ አስር ወይም አስራ አንድ ሰዓት እቆያለሁ፡ ስለዚህ ያ በእውነቱ ገና ነው። በ—በ—በጌታ መልዕክት ተባርካችኋል ዛሬ? በትክክል በልታችኋል? ነፍሳችሁን ይመግባል።

175 እግዚአብሔር ይባርካችሁ፡ ልጆቼ። በሙሉ ልቤ እንደምወዳችሁ፡ ታውቃላችሁ። እና አንዳንድ ጊዜ መንፈሱ ሲይዘኝ፡ ሁለቱንም ወገን ይቆርጣል… ቃሉም እንዲህ ነው፡ በሁለት-ወገን የተሳለ ስለታም ሰይፍ ነው። ሲገባም፡ ሲወጣም፡ ወደ ውጪም፡ በሁሉም አቅጣጫ፡ ይቆርጣል። የሚገርዘንም በዚያ መልኩ ነው። ሊንጠለጠልብን የማይገባ ነገር ግርዛት ይቆርጥልናል፡ የተረፈውን ሥጋ መቁረጥ ነውና።

176 አሁን፡ እንድታስተውሉ እፈልጋለሁ። ዛሬ ማታ በተሰጠ ትርጉም መንፈሱን ሰምታችኋልን? "ያንን ሞኝነትን አቁሙት!" ይህ ይገርዛል። ቅኖች ሁኑ! ሁላችንም ከመስመር እንወጣለን፡ እግዚአብሔር ግን ከእኛ ላይ ያለውን እብጠት እንዴት እንደሚላጭ ያውቃል። አይደለም'ዴ? በትክክል ያውቃል። በዚህም ደስ ይለኛል። እናንተስ?

177 ፒያኖ ተጫዋቿ አንቺ ነሽ? ቴዲ…. እዚህ አለ… ? የትም አይታየኝም። ይህ—ይህ ነው… ? ፍቃድሽ ከሆነ፡ በጣም ጥሩ፡ እህቴ። ልጅህ ናት፡ ወንድም ዳልተን? የሚስቴ-ልጅ-ናት። በጣም ጥሩ። እጅግ ድንቅ እመቤት፡ ክርስትያን በመሆንሽ ደስ ይለኛል። በጣም ጥሩ፡ የድሮ መሰናበቻ መዝሙራችን፡ ምን ነበር? ከመዘመራችን በፊት፡ እስኪ እንሞክረው፡ አሁን። እህቴ፡ አንድ ደቂቃ ብቻ፡ **የኢየሱስ ስም ከእናንተ ጋር ይሁን** ብለን ከመዘመራችን በፊት።

178 **የቤተሰብ ጸሎት አትርሱ** ስንቶች ታውቁታላችሁ? የቤተሰብ ጸሎት አላችሁ፡ በቤተሰብ ትጸልያላችሁ? መልካም ነው። አንድ ጊዜ እንዘምረው፡ ልክ እንደ ድሮ አሁን፦

የቤተሰብ ጸሎት አትርሱ፡
ኢየሱስን በዚያ ልበሱ፡
ሸክማችሁን ይወስደዋል እሱ፡
እነሆ፡ የቤተሰብ ጸሎት አትርሱ።

ወደዳችሁት ወይ? በድጋሚ እንዘምረው፡

የቤተሰብ ጸሎት አትርሱ፡
ኢየሱስን በዚያ ልበሱ፡ (አሁን፡ ጊዜ አላችሁ።)
ሸክማችሁን ይወስደዋል እሱ፡
እነሆ፡ የቤተሰብ ጸሎት አትርሱ።

179 [እንዲት እህት እንዲህ አለች፡ "ወንድም ብራንሃም፡ የሆነ ነገር መናገር እችላለሁ? "—እርታዒ።] አዎን ትችያለሽ፡ እህቴ። [እህቲቱ መናገር ጀመረች። ባዶ ቦታ በቴፕ ላይ።] እህት ናሽ፡ በጣም ጥሩ ነው። ኧረ፡ ፈቃደኛ ከሆንሽ፡

ብናምን ባንጠራጠርም፡ በእርግጥ ያወጣችኋል ከሁሉም፡
ብቻ ሸክማችሁን ወደ ጌታ ወሰዳችሁ ተውአቸው በዚያ።

ተውአቸው በዚያ፡ ተውአቸው በዚያ
ሸክማችሁን ወደ ጌታ ወሰዳችሁ ተውአቸው በዚያ።
ብናምን ባንጠራጠርም፡ በእርግጥ ያወጣችኋል ከሁሉም፡
ሸክማችሁን ወደ ጌታ ወሰዳችሁ ተውአቸው በዚያ።

180 የድሮ መዝሙሮችን አትወዷቸውም? እነሆ፡ እነርሱ... እነዚያ ሰዎች ያንን ሲያነቡ ብዕራቸውን አንስተው ከመንፈስ ቅዱስ ምሪት ተቀብለው እንደሆኑ አምናለሁ።

181 ልክ እንደ አይነ ስውሯ ፋኒ ክሮሰቢ የዚያን ጊዜ ዓለማዊ ሰዎች ዓለማዊ ዘፈኖችን እንድትጽፍ ሲሞክሩ፡ "ኧረ፡ ኃብታም ትሆኛለሽ፡" አሏት።

እውር እንደነበረች፡ ታውቃላችሁ። "ህይወቴን እና ችሎታዬን በሙሉ፡ ለክርስቶስ መሰዋዕት አድርጌዋለሁ፡" አለቻቸው። አለችም፡ "በ—በህይወቴ እና በሁለንተናዬ ስለ ክርስቶስ ባለ ዕዳ ነኝ፡" እንዲህ አለች...

182 እና እንደዚህ አይነት እድል ስላልተቀበለች እንደመበሳጨት አደረጋቸው። ክብሯን—አስጠብቃለች እንጂ፡ እንደ አቶ. ፕሪስሊ እና እንደሌሎቹ ብኩርናዋን አልሸጠችም። ስለዚህ እነርሱም—እነርሱም... እሷን—ትተዋት ሄዱ፡ እንዲ አሏት፡ "እንደዚህ ያለ ቦታ ካለ፡ ወደ መንግሥተ ሰማያት ስትገቢ፡" "አሁን እዚህ እንዳለሽበት ከሆንሽ፡ ዕውር ትሆኛለሽ፡" አሏት። "አንቺ ዕውር **ብትሆኚስ**፡" አሏት፡ "በምንሽ ታውቂዋለሽ? " አሏት፡

"ኧረ'ኔስ አውቀዋለሁ። ኧረ'ኔስ አውቀዋለሁ፡" አለች።

"አንቺ ዕውር ብትሆኚስ? አንቺ ዕውር ብትሆ**ኚስ**? " አሏት፡

"በምስማር የተወጉትን እጆቹ እዳብሳለሁ፡" አለች። ከዚያም ዘወር ብላ፡ ወደ ኋላ መሄድ ጀመረች እና፡ እንዲህ አለች፡-

አውቀዋለሁ፡ አውቀዋለሁ፡
ይቤዠኛል በጎኑም እቆማለሁ፡
አውቀዋለሁ፡ አውቀዋለሁ
በምስማር በተወጉት እጆቹ አሻራዎች።

183 ኢየሱሴ ሆይ፡ በእነዚያ ስለ እኔ በሚደሙ፡ በአምስት የከበሩ ቁስሎች፡ ያን ውድ ሰው እንዴት ልክደው እችላለሁ? እኔ ልሙት፡ እኔ ልሂድ... በማንኛውም

መንገድ እንድሄድ ተውኝ፡ ነገር ግን ያንን ለእኔ የሞተልኝን ያንን ውድ ደም አታስክዱኝ። አዎን።

184 እና ዛሬ ማታ ስትወጡ፡ **የኢየሱስን ስም ከናንተ ጋር ይሁን**፡ ያስፈልጋችኋል። እሺ፡ እህቴ። አሁን ሁላችንም፡ በአንድነት እንቁም።

... ስም ከናንተ ጋር ይሁን፡
የሀዘንና የዋይታ ልጅ፡
ደስታ እና ምቾት ይሰጣችኋል፡
በሄዳችሁበት አትለዩት።

ድንቅ ስም፡ (ድንቅ ስም!) ኦህ ውብ ስም (ኦህ ውብ ስም!)
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፡
ድንቅ ስም፡ (ድንቅ ስም!) ኦህ ውብ ስም!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።

አሁን አንገታችንን ደፍተን፡ በቀስታ እንዘምር፡-

ለኢየሱስ ስም እሰግዳለሁ፡
በእግሩ ስር እወድቃለሁ፡
የነገሥታት ንጉሥ እናክብር በሰማይ፡
ጉዟችን ሲጠናቀቅ ከምድር።

ድንቅ ነው፡ ኦህ ውብ ስም!
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ፡
ድንቅ ስም፡ ኦህ ውብ ስም! (ውብ ስም!)
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።

**የሰምርኔስ ቤተ ክርስትያን ዘመን** AMH60-1206

(The Smyrnaean Church Age)

**የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ተከታታይ ትምህርት**

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ ታሕሳስ 6፡ 1960፡ ማክሰኞ ማታ፡ በዩ.ኤስ.ኤ. ጀፈርሰንቪል፡ ኢንዲያና ከሚገኘው፡ ከብራንሃም ተበርናክል፡ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይስ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግስ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2023 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

# የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org